የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤቶች የሚመሩባቸው መርሆዎች እና ሕገ መንግሥቱ

(ክፍል አንድ)

1. የዐቃቤ ሕግ ምንነት (ትርጉም)

"ዐቃቤ ሕግ" የሚለው መጠሪያ የያዘው ሁለት ቃላትን ነው። "ዐቃቤ" የሚለው ቃል "ዐቀበ" ከሚለው የግዕዝ ቃል የመነጨ ሲሆን ትርጉሙም ጠበቀ ማለት ነው። ይህ የሚያስገነዝበው "ዐቃቤ ሕግ" ማለት "የሕግ ጠባቂ" ማለት መሆኑን ነው።[1]

ዐቃቤ ሕግ ስሙ እንደሚያመለክተው የሕግ ጠባቂ ወይም ሕግ አስከባሪ ማለት ነው። ማንኛውም የመንግሥት አካል በተለይ ሕግ አስፈጻሚው በተቋቋመበት አዋጅ በተለዩ በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሠረት የተቋቀመበትን ሕግ የማስፈጸም ግዴታ አለበት። ነገር ግን ዐቃቤ ሕግን ስንመለከት ከእነዚህ መንግሥታዊ አካላት የተለዩ ነው። ዐቃቤ ሕግ የሚያስከብረው የተቋቋመበትን አዋጅ ብቻ አይደለም፤ ሕግ አውጪው ያወጣቸው ሕጐች በሙሉ መከበራቸውን የመከታተል ኃላፊነት አለበት።

የዐቃቤ ሕግ ትርጉም ይህን ሲመስል በአገራችን በተለይ ዐቃቤ ሕግ የሚለው መጠሪያ የሚታወቀው ግን እላይ ካስቀመጥነው ትክክለኛ ትርጉም አንፃር ሳይሆን ወንጀል ለመፈጸሙ በቂ ማስረጃ ሲቀርብለት ወንጀሉን ፈጸመ በተባለው ሰው ላይ መንግስትን ወክሎ ክስ የማቅረብና መከራከር ተግባር ብቻ የያዘ ተቋም ተደርጐ ሲወሰድ ነው የሚታየው ።

ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ጉዳይ ዙሪያ ብቻ ሥልጣን ያለው አካል አድርግ የመውሰዱ ጉዳይ በተለይም የኮመን ሎው የሕግ ሥርዓትን በሚከተሉ አገሮች በብዛት የሚስተዋል ጉዳይ ነው። የኮመን ሎው አገሮችን በተለይም የአሜሪካን የሕግ ሥርዓት

[1] የፍትሕና የዴሞክራሲ ሥርዓት ሒደት በኢትዮጵያ፣1992፣አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ፣ ገጽ 350

የሚያንፀባርቀው በሕግ ሙያ ዙሪያ የምንጠቀምባቸውን ቃላት እና ሀረጎች ወይም ፅንሰ ሀሳቦች ለመተርጎም ብዙ ጊዜ የምንጠቀምበት ብላክስ ሎው የሕግ መዝገበ ቃላት "prosecutor" (also termed public prosecutor; state's attorney; public commissioner) የሚለውን ቃል " a legal officer who represents the state or federal government in criminal proceedings."[2] በማለት ይተረጉመዋል።

ከዚህ በላይ ለዐቃቤ ሕግ በመዝገበ ቃላቱ የተሰጠው ትርጉም ወደ አማርኛ በግርድፉ ሲመለስ "ዐቃቤ ሕግ ማለት በወንጀል ጉዳዮች የፌዴራል ወይም የክልል መንግስታትን ወክሎ የሚሰራ የሕግ ባለሙያ ነው" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። የዚህ የዐቃቤ ሕግ ትርጉም መሠረቱ የመንግሥትና የህብረተሰቡ መብትና ጥቅም ጉዳት ላይ ሊወድቅ የሚችለው በወንጀል ድርጊቶች በመሆኑ የመንግሥት ኃላፊነት ወንጀል የሚፈፅሙ ሰዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ መውሰድ ነው የሚል አመለካከትን የያዘ የአብዛኛው የኮመን ሎው አገራትን አቋም የሚያንፀባርቅ አካሄድ ነው። በኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት የዐቃቤ ሕግ ዋነኛ የሥራ ድርሻ የወንጀል ጉዳዮችን መከታተል ሲሆን ይህ ሊሆን የበቃውም የማህበረሰቡ የጋራ መብትና ጥቅም ሊነካ (ሊጠቃ) የሚችለው በወንጀለኞች ብቻ በመሆኑ ወንጀለኞችን ተከታትሎ በወንጀል እንዲጠየቁ በማድረግ የማህበረሰቡን መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ይቻላል በሚል እምነት ይመስላል።[3] በተነጻጻሪ የሲቪል ሎው የሕግ ሥርዓትን ስንመለከት ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ጉዳይ ዙሪያ ካለው የሥራ ድርሻ በተጨማሪ በፍትሐብሔርም ሰፊ የሥራ ድርሻ ያለው ሆኖ እናገኘዋለን። እንደ ሲቪል ሎው የሕግ ሥርዓት ተከታይ አገሮች ሁሉ በኢትዮጵያም የዐቃቤ ሕግ የሥራ ድርሻ የወንጀል ጉዳዮችን በመከታተል ዙሪያ ብቻ የተገደበ አይደለም።

ዐቃቤ ሕግ ሕግ አውጭው ያወጣው የወንጀል ሕግ በተጣሰ ጊዜ ሕጉን ወክሎ በችሎት የወንጀል ክስ የማቅረብና የማስቀጣት ኃላፊነት ያለበት ቢሆንም ይህ ከተሰጡት

[2] Black's Law Dictionary; 8th ed., 2004;p.1258
[3] ዮሴፍ ገ/እግዚአብሔር፣ የፍትሕና የዴሞክራሲ ሥርዓት ሒደት በኢትዮጵያ፣1992፣አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ፣ ገጽ 368

ተግባራት መካከል አንዱ የስራ ድርሻው ሲሆን ዐቃቤ ሕግ በዚህ ብቻ ሳይወሰን ከላይ እንደጠቀምነው ሕግ አውጭው ያወጣቸውን ማናቸውንም ሕጐች የማስከበር ሥልጣንና ኃላፊነት የተቀበለ አካል ነው፡፡ ስለሆነም በወንጀል ጉዳይ ምርመራ እንዲካሄድ ማድረግ (ወይም ምርመራውን ራሱ ማካሄድ)፣ የወንጀል ክስ አቅርቦ መከራከር ወ.ዘ.ተ. ለዐቃቤ ሕግ ከተሰጡት ተግባራት ውስጥ ከፊሉ ተብሎ ሊወሰድ የሚችል እንጅ የዐቃቤ ሕግ ሥራ በወንጀል ዙሪያ ብቻ የተገደበ አይደለም፡፡

2. <u>በኢትዮጵያ የዐቃቤ ሕግ ተቋም ታሪካዊ አመጣጥ አጭር ምልከታ</u>

በአገራችን የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ዕድገት ውስጥ የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ አስፈላጊነቱ ታምኖበት የተቋቋመው በ1934 ዓ.ም. ስለ ዐቃብያነ ሕግ አሻሻምና ቁጥጥር በወጣው አዋጅ ቁጥር 26/1934 ነው፡፡ ይህ አዋጅ ከፍተኛ የወንጀል ጉዳዮች ሳይቀሩ በግል ተበዳይ ወይም በቅርብ ዘመዶቹ ምርጫ ክስ የሚቀርብበትን ወይም ጉዳዩ በእርቅ የሚያልቅበትን ሁኔታ በመቀየር የወንጀል ጉዳይ በመንግሥት በተቋቋመ አካል እንዲመራ በማድረግ በኢትዮጵያ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በተለይም በሀገሪቱ ውስጥ የሕዝብን ፀጥታ የሚነኩ ሕጎችን የሚያስከብር እና በፍርድ ቤቶች ዘንድ በሚቀርብ ጉዳይ ክትትል የሚያደርግ አንድ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግና ሌሎች ዐቃብያነ ሕግ የያዘ በፍርድ ሚኒስትሩ የሚመራ ተቋም ተመሠረተ፡፡

በዐቃቤ ሕግነት ሥራ ታሪክ ሌላው ጉልህ ክስተት የታየው በ1980 ዓ.ም.ነው፡፡ በዚህ ወቅት ዐቃቤ ሕግ የመንግሥት አካላት፣ ሕዝባዊ ድርጅቶች፣ሌሎች ማህበራት፣ ባለሥልጣኖቻቸውና ማንኛውም ግለሰብ ሕግን ማክበራቸውንና የሕጉንም አንድ ወጥ አፈፃፀም የማረጋገጥ ሕገ መንግሥታዊ ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡[4] ይህ በሕገ መንግስት ደረጃ ጠቅለል ብሎ የተሰጠ ሥልጣን የኢ.ሕ.ዲ.ሪ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 11/1980 ዘርዘር ብሎ እንዲደነገግ የተደረገ ሲሆን በዚህም መሠረት የዐቃቤ ሕግ የሥራ ድርሻ ከምንጊዜውም በላይ ሰፍቶ የፍርድ ቤቶችን

[4] የኢ.ሕ.ዲ.ሪ. ሕገመንግሥት አንቀጽ 108(1)

ውሣኔ የመመርመር፣ እስር ቤቶችን መቆጣጠር እና ግለሰብ ወይም ንብረት እንዲያዝ ወይም እንዲፈተሽ ትዕዛዝ እስከመስጠት ደርሶ ነበር፡፡ ይህንን ሠፊ ሥልጣኑን መሠረት በማድረግ ሕጎች በየትኛውም አካል መከበራቸውን በማረጋገጥ ረገድ ዐቃቤ ሕግ የተጫወተው ሚና ዛሬም ድረስ በአዎንታዊ መልኩ የሚጠቀስ ሲሆን በሌላ በኩል ግን በፍርድ ሥራ ጣልቃ እንዲገባ በሕግ መፈቀዱና ይኸው ተግባራዊ ይሆን የነበረ መሆኑ በአሉታዊ መልኩ የሚነሳ ነው፡፡

በግንቦት ወር 1983 ዓ.ም. የተከሰተውን የመንግሥት ለውጥ ተከትሎ አገራችን በፌዴራል ሥርዓት በመዋቀሯ ቀደም ሲል የነበረው አንድ ወጥ የዐቃቤሕግ አደረጃጀት ተቀይሮ በክልል እና በማዕከል ተደራጅቶ እራሱን ችሎ ተዋቅሯል፡፡ ይህ አደረጃጀት የማዕከላዊ መንግሥትንና የክልል መንግሥታትን የወንጀል ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን ክፍፍል ተግባራዊ ለማድረግ ሥራ ላይ የዋለ ነው፡፡ ለዚህም የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የማዕከላዊ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤትን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 39/1985 ቀደም ሲል ዐቃቤ ሕግ በዳኝነት /በፍርድ/ ሥራ ላይ ጣልቃ እንዲገባ ያስችለው የነበረውን ሥልጣን ሲያስቀር በሌላ በኩል የግለሰቦችን መብትና የሕብረተሰቡን አጠቃላይ ጥቅም ለማስጠበቅ ወሣኝ የሆኑ ሥልጣንና ኃላፊነቱን ጠብቋል፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታም ክልሎች የየራሳቸውን የዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤቶች ያቋቋሙበት ሁኔታ ሊፈጠር ችሏል፡፡

አዋጅ ቁጥር 39/85ን የሻረው የዐቃብያነ ሕግ አዋጅ ቁጥር 74/1986 ለማዕከላዊ ዐቃቤ ሕግ የተሰጡትን ሥልጣንና ኃላፊነት ለፍትሕ ሚኒስቴር በማስተላለፍ ከጥቅምት 12/1986 ዓ.ም. ጀምሮ የማዕከለዊ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤትንና የፍትሕ ሚኒስቴርን በማዋሀድ አንድ መንግሥታዊ አካል አድርጓቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ እና በሌሎች ሕጎች የዐቃቤ ሕግ ሥልጣንና ኃላፊነትን አስመልክቶ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው የፌዴራል ዐቃቤ ሕግን የሚመለከቱ ሥልጣንና ተግባራት በዋናነት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባራት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 4/87 ተዘርዝረው የነበሩ ሲሆን አዋጁን የሻረው አሁን ሥራ ላይ ያለው አዋጅ ቁጥር 471/98 አንቀጽ 23 በአብዛኛው ቀደም ሲል ከነበረው አዋጅ ጋር

ተመሳሳይ የሆነ ሥልጣንና ተግባር ለፍትሕ ሚኒስቴር (ለፌዴራል ዐቃቤ ሕግ) ይሰጠዋል።[5]

3. ዐቃብያነ ሕግ ሊከተሏቸው የሚገቡ መርሆዎች እና ሕገ መንግሥቱ

የተለያዩ የሥራ ዘርፎች እንደየሥራ ጠባያቸው ሥራውን በአግባቡ ለማከናወንና ህብረተሰቡ የሚጠብቀውን አገልግሎት ለመስጠት የሚከተሏቸው መርሆዎች ወይም መመሪያዎች አሏቸው። አንዳንዶቹ መርሆዎች አብዛኛዎቹ የሥራ ዘርፎች የሚከተሏቸው መመሪያዎች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በተለይ በአንድ የሥራ ዘርፍ ተፈጻሚነት ያላቸው ናቸው።

ከዐቃብያነ ሕግ ሥራ አንጻር ነገሩን ስንመለከተው ዐቃብያነ ሕግ ሥራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት ሊፈፅሟቸው የሚገቡ ተግባሮችና ሊከተሏቸው የሚገቡ በመርሆነት ሊወሰዱ የሚችሉ ነገሮችን እናገኛለን። እነዚህ መርሆዎች በአንድ ሰነድ ወይም በአንድ ራሱን በቻለ ሕግ ተካተው የምናገኛቸው ሳይሆኑ ተሰበጣጥረው የምናገኛቸው ነገር ግን ዐቃብያነ ሕግ ሊመሩባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው። እነዚህ ጉዳዮች ብዛት ያላቸው ቢሆኑም ከዐቃብያነ ሕግ ሥራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ዋና ዋና የሚባሉ መርሆዎች ከዚህ ቀጥሎ ተመልክተዋል።

3.1. ለአገሪቱ ሕገ መንግሥት ታማኝ መሆን

ዐቃቤ ሕግ የሚሰራው በሕግና በሕግ መሰረት ብቻ ነው። የግል እምነቱና ፍላጎቱ ከሕጉ ጋር የሚጋጭ እንኳ ቢሆን በግል ስሜቱ ሳይሸነፍ ሕጉን ተግባራዊ

[5] ለፍትሕ ሚኒስቴር የተሰጡት ሥልጣንና ተግባራት ሁሉ መስሪያ ቤቱ በፌዴራል ዐቃቤ ሕግነት ሥልጣኑ (capacity) የተሰጠው ተብሎ ሊወሰድ አይችልም። አንዳንዶቹ የመሥሪያ ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት ተቋሙ የፍትሕ ሚኒስቴር በመሆኑ ምክንያት የተሰጡ ናቸው ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ። እነዚህ ሥልጣንና ተግባራት የትኞቹ ናቸው የሚለውን ለመለየት ምናልባት በአብዛኛዎቹ አገራት የፍትሕ ሚኒስቴር የሚኖረውን ሥልጣንና ተግባራት ማየት ተገቢ ሊሆን ይችላል። በክልል ደረጃም እንደዚሁ ለፍትሕ ቢሮዎች የትኞቹ ሥልጣንና ተግባራት ናቸው በዐቃቤ ሕግነት ሥልጣናቸው የተሰጣቸው የሚለውን ለማወቅ በፌዴራል ደረጃ ያለውን ሁኔታ መከተሉ የሚያስኬድ ይመስላል።

ማድረግ ይጠበቅበታል። ሕገ መንግሥቱ ደግሞ የአገሪቱ የበላይ ሕግ ነው።[6] የፌዴራል ዐቃብያነ ሕግ መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር 44/91 አንቀጽ 4(ለ) ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ ሆኖ የሚሾም ሰው ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት ታማኝ የሆነ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል።

ስለዚህም ምንም እንኳን ሕገ መንግስቱን ተግባራዊ ማድረግ የሁሉም ዜጋና ባለሥልጣን ግዴታ ቢሆንም በዐቃቤ ሕግ የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ የሕገ መነግስቱ የበላይነት ከፍተኛ ትርጉም ያለው ጉዳይ ነው። የሕጎች ሁሉ የበላይ ለሆነው ሕግ ታማኝ ያልሆነ ዐቃቤ ሕግ በሕግ መሰረት ሥራውን ሊያከናውን ይችላል ብሎ መገመት የሚቻል ነገር አይሆንም። ሥለዚህ ሕገ መንግሥቱንና የሕገ መንግስቱን መርሆዎች የማይቀበልና ተግባራዊ የማያደርግን የሕግ ባለሙያ በዐቃቤ ሕግነት ሥራ ውስጥ እንዲሰራ ማድረግ አግባብነት አይኖረውም።

እዚህ ላይ መስተዋል ያለበት ነጥብ ግን ይህ መርህ ከአንድ ዐቃቤ ሕግ የፖለቲካ አመለካከት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት የሌለው የመሆኑ ጉዳይ ነው። ለሕገ መንግስቱ ታማኝ መሆን ማለት የገዢውን ፓርቲ የፖለቲካ አስተሳሰብ መደገፍ ማለት አይደለም። ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ የፈለገውን የፖለቲካ አስተሳሰብ መከተል ይችላል። ነገር ግን የትኛውንም የፖለቲካ አስተሳሰብ ቢከተልም ለሕገ መንግስቱ ታማኝ መሆኑን ጥያቄ ወስጥ ማስገባት የለበትም። በዚህም መሰረት የዐቃቤ ሕግነት ሥራውን በሚያከናውንበት ወቅት የግል እምነቱንና የፖለቲካ አመለካከቱን ወደ ጎን በመተው ለሕገ መነግስቱ ታማኝ በመሆን ኃላፊነቱን በሕግ እና በሕግ መሰረት ብቻ ማከናወን ይጠበቅበታል።

3.2. <u>የሕጋዊነት መርህን ማክበር</u>

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው ዐቃቤ ሕግ ለሕገ መንግሥቱ ታማኝ የሆነ መሆን አለበት። ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያለው ሌላው ጉዳይ ደግሞ በተለይም ከወንጀል ጉዳይ ጋር በተያያዘ ዐቃቤ ሕግ የሕጋዊነት መርህን አጥብቆ መከተል ያለበት መሆኑ ነው። በዚህም መሠረት በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተገለፀ በስተቀር ለአንድ ወንጀል በወንጀል

[6] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9(1) "ሕገ መንስቱ የበላይ ሕግ ነው።ማኛውም ሕግ፣ልማዳዊ አሰራር እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግስት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም" በማለት ይደነግጋል።

ሕጉ ልዩ ክፍል ከተደነገገው የቅጣት ወሰልና ጣራ ውጭ ቅጣት ሊጣል አይችልም። እንዲሁም ለአንድ የወንጀል ድርጊት ሊጣል የሚችለው ቅጣት የሚወሰነው ወንጀሉ ከተፈፀመበት ወቅት አስቀድሞ በተደነገገ የወንጀል ድንጋጌ በተመለከተው መሠረት ነው። ከዚህ አኳያ በአገሪቱ የሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ የሆነው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 22 "ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈፀመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈፀሙ ወይም አለመፈፀሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም። እንዲሁም ወንጀሉን በፈፀመበት ጊዜ ለወንጀሉ ተፈጻሚ ከነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወሰንም" ይላል።

ይህ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ሁለት ዓይነት መሠረታዊ ውጤቶችን ያስከትላል። እነዚህም አንድ ድርጊት በሚፈፀምበት ወቅት ድርጊቱ በጊዜው የማያስቀጣ ከነበረ ይኸው አስቀድሞ የተፈፀመው ድርጊት ከጊዜ በኋላ በወጣ ሕግ ወንጀል ነው ሊባል አይችልም። በተጨማሪም ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት ወንጀል ቢሆንም እንኳ ወንጀለኛው መቀጣት ያለበት ድርጊቱ በተፈፀመበት ወቅት ድርጊቱ በሚፈፀምበት ወቅት ተፈጻሚነት የነበረው የወንጀል ሕግ በደነገገው የቅጣት ጣራ መሠረት መሆን አለበት። ስለዚህም ከድርጊቱ በኋላ የወጣ ሕግ የቅጣት ጣራውን ከፍ ቢያደርገው ይህ ቅጣት ሕጉ ከመታወጁ በፊት ለተፈፀመ ወንጀል ተፈጻሚ መሆን የለበትም።

በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ ሕግ ጠባቂ እንደመሆኑ የሕጋዊነት መርህን አጥብቆ ማክበር ይጠበቅበታል። ከዚህም አኳያ ለምሳሌ አንድን ድርጊት ወንጀል የሚያደርግ ግልፅ የወንጀል ሕግ ሳይኖር በማመሳሰል (by analogy) በአንድ ተከሳሽ ላይ የወንጀል ምርመራ እንዲጣራበት ከማዘዝ ወይም የወንጀል ክስ ከማቅረብ መቆጠብ አለበት።

3.3. <u>በሰዎች መካከል ልዩነት አለማድረግ</u>

በቅድሚያ ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ምርመራ መዛግብትን በመመርመር ክስ ለማቅረብ ወይም ክስ ላለማቅረብ ውሳኔ በሚሰጥበት ወቅትም ሆነ በክርክር ሂደት ሁሉ በሕገ መንግስት አንቀጽ 25 የተደነገገውን የሰዎችን በሕግ ፊት እኩል መሆንና እኩል

የሕግ ጥበቃ የማግኘት መብት ማክበር ይገባል። የዐቃብያነ ሕግ ሚናን አስመለክቶ እ.ኤ.አ በ1990 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀደቀው ሰነድም (guideline) እንዲሁ "prosecutors shall carry out their functions impartially and avoid all political, social, religious, racial, cultural, sexual or any other kind of discrimination"[7] በማለት ይደነግጋል። ከዚህ አንጻር ዐቃብያነ ሕግ ምርመራ በሚያጣሩበት ወይም ምርመራ እንዲጣራ በሚያዙበት ወቅት፣ ክስ ለማቅረብ ወይም ላለማቅረብ ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ፣ በፍርድ ቤት ሙግት ወቅት፣ ይግባኝ ለማለት ወይም ላለማለት በሚወስኑበት ጊዜ የተከሣሹን ዘር፣ ቋንቋ፣ ኃይማኖትና የፖለቲካ አመለካከቱን እንደሁም የማህበራዊ አቋሙን መሠረት በማድረግ ልዩነትና አድሎ መፈፀመ የለባቸውም። በተከሣሾች ላይ የሚታዩት እንደዚህ ዓይነቶቹ ልዩነቶች ዐቃቤ ሕጉ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ፍፁም ቦታ ሊሰጣቸው ወይም ሊኖራቸው አይገባም።

3.4. <u>ለሕዝብ ጥቅም ቅድሚያ መስጠት</u>

ዐቃቤ ሕግ ለፍትሕ፣ ለእውነትና ለእኩልነት የቆመ መሆን አለበት። በወንጀል ዙሪያ ጉዳዩን ካየነው የሕዝብና የመንግስት ፍላጐት ወንጀል አድራጊዎች ለፈጸሙት ድርጊት ተመጣጣኝ ቅጣት እንዲያገኙና ንጹሀን ሰዎች ባልፈጸሙት ድርጊት አለአግባብ እንዳይንገላቱ መከላከል ነው። በአንድ በኩል ወንጀል አድራጊዎች ከተጠያቂነት እንዳያመልጡ የህዝብ ጥቅም ይጠይቃል። በሌላ በኩል ደግሞ ንፁሀንን ከአጥፊዎች የመለየቱ ሂደት ችግር ያለበት ሆኖ ያላጠፉ ሰዎች አጥፊ ናቸው ተብለው እንዳይጠየቁ ወይም የመለየት ሂደቱ አግባብ ያልሆነ ጉዳት በንፁሀን ላይ እንዳያደርስባቸው ያስፈልጋል። በአጥፊዎችም ላይ ቢሆን ፍትሐዊ የሆነ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ብቻ ሳይሆን በፍትሐዊ መንገድ ጉዳያቸው እንዲታይ ህብረተሰቡ ይፈልጋል። ለዚህም ነው "ፍትሕ መስጠት ብቻ ሳይሆን ፍትሕ ሲሰራም መታየት አለበት" የሚባለው።[8]

ከዚህ አኳያ ዐቃቤ ሕግ በሥራ እንቅስቃሴው ወቅት ዓላማ ማድረግ ያለበት ተከሣሹን ጥፋተኛ ማሰኘትንና ማስቀጣትን ሳይሆን እውነት እንዲወጣ ማድረግን ነው።

---

[7] Guidelines on the Role of Prosecutors Adopted by the Eighth United Nations Congress on the Prevention of Crime and the Treatment of Offenders, Havana, Cuba, 27 August to 7 September 1990

[8] ፋሲል ናሆም (ዶ/ር)፣ ቅጣትና ጎብረተሰብ፤ዕድገታዊ አመለካከት፣የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት፣ቮልዩም 12፣ 1974፣ ገጽ 25

በዚህም መሠረት ተከሣሹን ጥፋተኛ ለሚያሰኘው ብቻ ሳይሆን ከቅጣት ሊያድነው ለሚችሉ ግላዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ሁሉ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ሕብረተሰቡ የሚቀበለው እውነት እንዲወጣ መጣር አለበት፡፡ በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ በግለሰቦች ወይም ቡድኖች ፍላጎት እና በመገናኛ ብዙሃን ግፊት ክስ ሊመሠርት ወይም ሌላ ውሳኔ ሊሰጥ አይገባም፡፡

ዐቃቤ ሕግ ተከሣሹን የሚጠቅም ማስረጃ በእጃቸው ገብቶ ከሆነ ይህንኑ ማስረጃ ለተከሣሹ አሳልፎ በመስጠት፣ ወይም ማስረጃው የሚገኝበትን ቦታ የሚያውቁ ከሆነ ተከሣሹ እንዲያገኘው በማድረግ ይህን ሐቅ የማውጣት ተልዕኳቸውን በብቃት መወጣት አለባቸው፡፡ ይህ ሣይሆን ቢቀር በመሠረቱ ለመክሰስ በሰለጠነና ተከሳሹን ጥፋተኛ የሚያሰኙ ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ ሰፊ ዕድል ባለውና ራሱን ለመከላከል ውሱን አቅም ባለው ግለሰብ መካከል የሚደረግ ሙግት ሚዛናዊ ሊሆን የማይችል ብቻ ሳይሆን ለትክክለኛ ፍትሕ የማይረዳና ንፁሀን ያለጥፋታቸው ወይም ከጥፋታቸው በላይ ሊቀጡ የሚችሉበትን ዕድል መፍጠሩ የማይቀር ነው፡፡

እንዲሁም ዐቃቤ ሕግ ክስ ከመሠረተ በኋላ በክርክር ሂደት የተከሣሹን ንፁህነት ከተረዳ ወይም በተከሣሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሣኔ ለማሰጠት የማይችል መሆኑን ከተገነዘበ የተከሣሹን ፍርድ ቤት መመላለስ እንደ ግብ በመቁጠር ወይም በግዴለሽነት በክርክሩ መቀጠል የለበትም፡፡ ይልቁንም አግባብነት ያለው የፍርድ ቤት አካሄድ መርሆዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት በሥራ ላይ የሉትን ሕጎች መሠረት አድርጎ ክሱን ማንሳት ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አንፃር በአገራችን ሰውን ያውም ያለበቂ ማስረጃ ከመክሰስ ይልቅ የቀረበን ክስ ማንሳት እንደ ከፍተኛ ውሣኔ ስለሚቆጠርና ከሥነ ምግባር ችግር ጋርም ለማያያዝ ስለሚሞከር ዐቃብያነ ሕግ የጥፋተኝነት ውሳኔ ለማሰጠት የማይችሉ መሆኑን እየተረዱም ቢሆን እንኳን ክሱን ሲያነሱ አይታይም፡፡ ነገር ግን የሕዝብ ጥቅም የሚጠበቀው በማስረጃ የተረጋገጠውንና የታመነበትን ነገር ይዞ በመከራከር አይደለም፡፡ እንዲያውም እንዲህ ዓይነቱ ተግባር የሕብረተሰቡን አጠቃላይ ጥቅም የሚጻረር ነው፡፡

3.5. ምስጢር መጠበቅ

የዐቃብያነ ሕግ ሚና አስመለክቶ እ.ኤ.አ በ1990 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የፀደቀው ሰነድ (guideline) "prosecutors shall keep matters in their possession confidential, unless the performance of duty or the needs of justice require otherwise."[9] ዐቃቤ ሕግ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ሁሉ አግባብነት ያለው የፍርድ አካሄድ መርሆዎችን፣ የተጎጂዎችንና የምስክሮችን ሕጋዊ ጥቅም ወይም ተቀባይነት ያላቸውን ሥጋቶች ግምት ውስጥ በማስገባት በሥራው አጋጣሚ በእጁ የገቡትን መረጃዎች በምስጢር መጠበቅ ይኖርበታል። በተለይም በዝግ ችሎት እንዲታዩ ሕግ የግድ በሚላቸው የወንጀል ጉዳዮች ዐቃቤ ሕግ በምንም ዓይነት ሁኔታ ስለጉዳዩ ከፍርድ በፊት በመገናኛ ብዙሀንም ሆነ በሌላ መንገድ መግለጫ መስጠት አይኖርበትም።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ወጣት ጥፋተኞችን በሚመለከት ፍርድ ቤት ነገሩን ሁሉ የሚሰማው በዝግ ችሎት ስለመሆኑ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ተመልክቶ እናገኘዋለን።[10] ነገሩ በሚሰማት ጊዜ እንዲገኙ የሚፈቀድላቸው ሰዎች ወላጆች፣ ምስክሮች፣ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ሞግዚት ወይም የበጎ አድራጎት አባል (ምናልባት ልጁ የሕጻናት ማሳደጊያ ድርጅቶች ውስጥ ይኖር ከነበረ) ብቻ ናቸው። ለአካለ መጠን ባልደረሱ ወጣቶች ላይ የሚቀርበው ክስ በዝግ ችሎት እንዲሰማ ሕጉ የሚያዝበት ምክንያት የጉዳዩ መሰማት ምስጢር ሆኖ እንዲጠበቅ ለማድረግ ይመስላል። ለአካለ መጠን ያልደረሰው ወጣት በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ቢገኝም ባይገኝም የነገሩ መሰማት በተቻለ መጠን በምስጢር የሆነ እንደሆነ ተከሳሹ ወደ ህብረተሰቡ ሲመለስ በቀላሉ ሊዋሀድ ይችላል።

በተመሣሣይ ሁኔታ በወንጀል ጉዳይ የዐቃቤ ሕግ ምስክር ሆኖ ለመመስከር ፈቅዶ የቀረበ ሰው በዚህ አድራጎቱ ከየትኛውም አቅጣጫ ጉዳት ይደርስብኛል ብሎ ካመነ ዐቃቤ ሕግ ከፍርድ መድረክ ውጪ ስሙንና የሚመሰክርበትን ጭብጥ ከመግለፅ መቆጠብ ይኖርበታል።

---

[9] Guidelines on the Role of Prosecutors Adopted by the Eighth United Nations Congress on the Prevention of Crime and the Treatment of Offenders, Havana, Cuba, 27 August to 7 September 1990

[10] የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 176(1)፣

3.6. <u>አዎንታዊ ልዩነቶችን ማክበር</u>

ዐቃብያነ ሕግ በሕገ መንግሥቱና በሌሎች ዝርዝር ብሔራዊ ሕጎች ስለ ወጣት አጥፊዎች የተደነገጉትን የጥበቃ ሥርዓቶች ማክበር አለባቸው፡፡ በተለይም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ "ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ... የሕፃናት ደህንነት በቀዳሚትነት መታሰብ አለበት" በሚል የተደነገገውን ዐቃብያነ ሕግ ልዩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር በአገራችን ወጣት ጥፋተኞች የወንጀል ድርጊት ፈፅመዋል ተብለው ሲጠረጠሩ የወንጀል ምርመራ የሚደረግባቸውም ሆነ በዐቃቤ ሕግ ክስ የሚቀርብባቸው የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚያዘውና መብቶቻቸውን በሚያከብር ሁኔታ ነው ለማለት አይቻልም፡፡

በወነጀለኛ መቅጫ ሕጋችን በግልፅ እንደተደነገገው ለአካለ መጠን ባልደረሱ ወጣቶች ላይ የሚቀርብ የወንጀል ክስ የሚመራው በሥነ ሥርዓት ሕጉ ከቁጥር 171 እስከ ቁጥር 180 ባሉት ድንጋጌዎች ማለትም ወጣት ጥፋተኞችን በሚመለከተው በልዩው ሥነ ሥርዓት መሠረት ነው፡፡

ለአካለ መጠን ያልደረሰ ወጣት የወንጀል ተግባር ፈጽሟል ተብሎ ሲጠረጠር ወድያውኑ መቅረብ ያለበት በቅርቡ ወደሚገኘው የወረዳ ፍርድ ቤት (ከፌዴራል ፍርድ ቤቶች አወቃቀር አንጻር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተብሎ ሊወሰድ ይችላል) ነው፡፡ ለአካለ መጠን ያልደረሰውን ወንጀል አድራጊ ለፍርድ ቤቱ ሊያቀርቡ የሚችሉትን በሚመለከት ፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ፣ ወላጆቹ ወይም ሞግዚቱ ሊሆን እንደሚችል የተመለከተ ሲሆን ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳ ፍርድ ቤትም መፈፀም ያለባቸውን እንደ ክሱን የመመዝገብና የፖሊስ ምርምራ ሂደቱን እንደ መቆጣጠር ዓይነት ሥራዎችን ካከናወነ በኋላ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን ያለው ከሆነ እዚያው ጉዳዩን ማየት ይቀጥላል፤ የወንጀል ክሱን የመስማት ሥልጣን ከሌለው ግን ሥልጣኑ ወዳለው ፍርድ ቤት ያስተላልፈዋል፡፡

ወጣቱ ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ ቤተሰብ ካልቀረበ እንዲጠራ ፍርድ ቤቱ ማድረግ ያለበት ሲሆን ተጠርቶ ቤተሰብ ባልቀረበ ጊዜ እንዲሁም ወጣቱ የተከሰሰበት ጉዳይ በሞት ወይም ከአስር ዓመት በላይ በሆነ የፅኑ እስራት ቅጣት በሚያስከትል ወንጀል የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጠበቃ ለአካለ መጠን ላልደረሰው ወጣት ተከሳሽ እንዲቆምለት ማድረግ ይኖርበታል (የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.174)፡፡

ለአካለ መጠን ያልደረሰው ወጣት ተይዞ ከቀረበለት በኋላ በወጣቱ ላይ የቀረበውን ክስ ወይም የክስ አቤቱታ የሚመዘግበውና ተገቢ መስሎ የታየውንም ማናቸውንም ምርመራ ፖሊስ እንዲያደርግ የሚመራው ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህም መሰረት ካልፈቀደ በስተቀር የተከሳሹን ተይዞ መቆየት የሚመለከቱ እንደ አስገዳጅ የሕክምና ምርመራና ቃልን መቀበል ያሉ የምርመራ እርምጃዎችን በራሳቸው ሥልጣን ፖሊሶች ሊወስዱ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም ከወረዳው ፍርድ ቤት አስቀድሞ ፈቃድ ሳያገኙ ይህን መሰል እርምጃ መውሰድ የሚችሉ ከሆነ ለአካለ መጠን ባልደረሱ ወጣቶች ላይ የሚፈፀም የፖሊሶችን የመያዝ ተግባር ለማስወገድ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 172ትን ጠቃሚ ዓላማ ዋጋ እንዳይኖረው የሚያደርግ ስለሚሆን ነው፡፡[11] ስለሆነም ፖሊስ አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ ከያዘ ወድያውኑ ፍርድ ቤት ማቅረብ ያለበት ሲሆን ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ሕጉ በፖሊስ ምርመራው ላይ ሙሉ ሥልጣን ለፍርድ ቤቱ ይሰጠዋል፡፡ ወጣቱ ተመልሶ ለፖሊስ ተላልፎ አይሰጥም፡፡ ከዚያ ይልቅ ጉዳዩ ቀጠሮ መስጠትን የሚጠይቅ ወይም ወደ የበላይ ፍርድ ቤት መቅረብ የሚገባው ሆኖ ፍርድ ቤቱ ሲያገኘው ጉዳዩ በሚሰማበት ጊዜ ለሚያቀርቡ ለወጣቱ ወላጆች፣ ለዘመድ ወይም ለሞግዚቱ ወ.ዘ.ተ. ለአካለ መጠን ያልደረሰው ወጣት ተላልፎ እንዲሰጥ ሕጉ ያዛል፡፡[12] ይህም የሚሆንበት ምክንያት ለአካለ መጠን ያልደረሱ ወጣቶች ጉዳያቸው ታይቶ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ታስረው እንዳይቆዩ በማድረግ ሕጉ ወጣት ጥፋተኞችን ወደ መልካም ሰውነት ለመመለስ ያለውን ዓላማ የሚጻረር ሁኔታ እንዳይፈጠር ለማስቻል ነው፡፡

[11] ስታንሊ ዜድ ፊሸር "በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት በወጣት ጥፋተኞች ላይ" የኢትዮጵያ ሕግ መጽሔት7፡1 ገጽ 64-5

[12] የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ቁጥር 172(4)፣

መደበኛ በሆኑ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ለመክሰስ ወይም ላለመክሰስ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ዐቃቤ ሕግ ነው፡፡ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ሰዎችን አስመልክቶ በሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ግን በወ/መ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 173 ላይ እንደተመለከተው ጉዳዩ ከአስር ዓመት በላይ በሆነ ፅኑ እስራት ወይም በሞት የሚያስቀጣ በሚሆንበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ዐቃቤ ሕግ የክስ ማመልከቻውን አዘጋጅቶ እንዲያቀርብ ያዛል በማለት የሚደነግግ ሲሆን ይህ አቀራረብ በሌሎች ጉዳዮች ላይ ግን አስቀድሞ ለፍርድ ቤቱ የሚቀርበው ክስ ወይም አቤቱታ እንደ ክስ ማመልከቻ ሆኖ እንደሚያገለግልና መደበኛ በሆነው ዓይነት መልኩ የክስ ማመልከቻ በዐቃቤ ሕግ በኩል ተዘጋጅቶ መቅረብ የሚያስፈልግ አለመሆኑን የሚያመላክት ከመሆኑም ባሻገር በሥነ ሥርዓት ሕጉ አንቀጽ 108 ላይ ለአካለ መጠን ባልደረሱ ወጣቶች ላይ የሚቀርበው ክስ በመደበኛው የክስ ማመልከቻ አቀራረብ ሥርዓት እንደማይሸፍን ከተመለከተው አንጻርም በወጣቱ ላይ ክስ ሊቀርብ ይገባ ወይም አይገባ እንደሆነ መወሰን የሚችለው ፍርድ ቤት ስለመሆኑ መገመት የሚያስችል ነው፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ መሠረት በወጣት ጥፋተኛ ላይ የሚደረገው የወንጀል ምርመራም ሆነ መደበኛ ክስ ሊቀርብ የሚችለው በፍርድ ቤት ትዕዛዝና መመሪያ መሆኑ የተደነገገ ቢሆንም[13] ፖሊስ ይህን ሥርዓት ሳይከተል ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ወጣቶችን በራሱ ጊዜ አስሮ የሚመረምርበት ሁኔታዎች የመኖራቸውን ያህል ዐቃቤ ሕግም የፍርድ ቤቱን ፈቃድ ሳይጠይቅ በማናቸውም የወንጀል ጉዳዮች ላይ መደበኛ ክስ እያዘጋጀ ለፍርድ ቤት ሲያቀርብ ይታያል፡፡

4. <u>የዐቃቤ ሕግ መሠረታዊ ተልዕኮ</u>

አንድ አገር ሕልውናውን ጠብቆ ለመቆየት እንዲችልና ፈጣንና ሁለንተናዊ ዕድገት እንዲያመጣ ወሳኝ የሆኑ በርካታ ጉዳዮችን ማንሳት ቢቻልም ማህበረሰባዊ ፀጥታና መረጋጋት እንዲሁም በዜጐችና በመንግስት መካከል ሊኖር የሚገባው መተማመን በግንባር ቀደምትነት ይጠቀሳሉ፡፡

[13] የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 171-180

እነዚህን ሁኔታዎች ተሟልተው እንዲገኙ ማድረግ በመሠረቱ የመንግሥት ግዴታ ሲሆን መንግሥት ግዴታውን የሚወጣው የሚጠበቅበትን የሕግ አውጪነት፣ የሕግ አስፈጻሚነት እና የህግ ተርጓሚነት ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ሲችል ነው፡፡

በዚህም መሠረት ሕግ አውጪው የሚያወጣቸው ሕጐች በራሳቸው ወይም ወደ ተግባር ሲተረጐሙ የማሕበረሰቡን ፀጥታና መረጋጋት እንዲሁም በዜጐችና በመንግሥት መካከል ሊኖር የሚገባውን መተማመን ሊጥሱ ወይም ሊሸራርፉ የማይችሉ መሆናቸውን ብቻ ሣይሆን በተቃራኒው ፀጥታና መረጋጋትን የሚያመጡና ግንኙነቱን ወደ ተሻለ ደረጃ የሚያሳድጉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

ሕግ ተርጓሚውም በበኩሉ በዳኝነት ሥራ አካሄዱና በሚሰጠው ውሳኔ አጠቃላይ የሆነውን የመንግሥት መሰረታዊ ተልዕኮ ግምት ውስጥ ማስገባትና ይህንኑ ተፈጻሚ ለማድረግ የመሥራት ኃላፊነት አለበት፡፡

ሕግ አስፈጻሚውም እንደዚሁ በሕግ የተሰጠውንና የተጣለበትን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ይኖርበታል፡፡ የሕግ አስፈጻሚው አካል የሆነው ዐቃቤ ሕግ ከዚህ አንጻር እንዲፈጽም የሚጠበቅበት ፀጥታና መረጋጋት እንዲሁም በዜጐችና በመንግሥት መካከል ሊኖር የሚገባውን መተማመን ተጠብቆ እንዲቆይ ሕግን አክብሮ መሥራት ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሕግን አክብረው መስራታቸውን መከታተልና ሕግን ጥሰው የሚገኙትን ለፍርድ ማቅረብ ነው፡፡

በሌላ አነጋገር የዐቃቤ ሕግ ዋንኛ ተልዕኮ ሕግን አክብሮ ኃላፊነቱን መወጣት ብቻ ሳይሆን የመንግሥትንና የሕዝብን መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ እንዲሁም ወንጀለኞችን ለፍርድ በማቅረብ ተገቢውን ቅጣት እንዲያገኙ ማድረግ ናቸው፡፡ በእርግጥ የወንጀል ድርጊት የሚፈጸመው በአመዛኙ በግለሰብ ላይ ቢሆንም ወንጀል አድራጊዎችን ለፍርድ ማቅረብ ከሕዝብ አጠቃላይ ጥቅም የሚመነጭ ነው፡፡ ስለዚህም በሕግ አሰፈጻሚው አካል ሥር ተደራጅተው ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ አንደኛው የሆነው ዐቃቤ

ሕግ የሕግ የበላይነት የማረጋገጥ እንዲሁም ሕጐች ሁሉ በአግባቡ መተግበራቸውን የመከታተል ተልዕኮ አለው፡፡

በዚህም መሠረት ዐቃቤ ሕግ የመንግሥትንና የሕዝብ መብትና ጥቅም ለማስከበርና የሕግን ተፈፃሚነት ለማረጋገጥ እንዲሁም የሕግ የበላይነትና ልዕልና እንዲረጋገጥ ለማድረግ በአስፈጻሚው የመንግሥት ክፍል ሆኖ አስፈጻሚው አካል ሕግ በሚያስፈፅምበት ወቅት ሕግና ሥርዓትን በተከተለ አኳኋን ተግባሩን እየተወጣ መሆኑን የመቆጣጠር፣ ሕግ የተላለፈውን ለፍርድ የማቅረብ ተልዕኮ ያለው ሲሆን ሌሎች ሰዎችም እንዲሁ ሕግን በመተላለፍ የሕዝብንና የመንግሥትን መብትና ጥቅም የሚነካ ተግባር ፈፅመው ሲገኙ በወንጀል ወይም/እና በፍትሐብሔር የሚያስከስሳቸው በቂ ምክንያት መኖር ወይም አለመኖሩን በመመርመርና ውሳኔ በመስጠት እስከ መጨረሻው ፍርድ ሰጭ አካል ድረስ የሕግ መጣስ ተግባር የፈፀመው ሰው ተገቢውን ፍርድ እንዲያገኝ የመከራከር ኃላፊነት አለበት፡፡

5. <u>የዐቃቤ ሕግ ሥልጣንና ኃላፊነት ከሌሎች አገሮች ተሞክሮ አንጻር</u>

የዐቃቤ ሕግ ሥልጣንና ኃላፊነት በተለይም በወንጀል ጉዳይ ዙሪያ ምን እንደሚመስል ከሌሎች አገሮች ተሞክሮ እያነፃፀርን ቀጥለን የምንመለከት ሲሆን ለንፅፅር እንዲያመች የዐቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባርን ከተለያዩ አጠቃላይ ከሆኑ የዐቃቤ ሕግ ሥራዎች አንፃር ለማየት ተሞክሯል፡፡

5.1. <u>በምርመራ ሥራ ላይ የዐቃቤ ሕግ ሥልጣንና ኃላፊነት</u>

በአንዳንድ በተለይም የኮመንሎው የሕግ ሥርዓትን በሚከተሉ አገሮች የወንጀል ሥርመራ የፖሊስ ብቸኛ (exclusive) ሥልጣን ሲሆን በምርመራ ተግባር ላይ ዐቃቤ ሕግ እንዲሳተፍና ምርመራ እንዲያካሄድ አይፈቀድለትም፡፡ ይህን የህግ ሥርዓት እና

ክስ በሚመሰርተው ዐቃቤ ሕግ መካከል ግልፅ የሆነ የሥልጣን ክፍፍል (Separation of functions) ይስተዋላል፡፡

በካናዳ ዐቃቤ ሕግና ፖሊስ የተለያዩ ሚና ያላቸው ሲሆን ቢያንስ በሕግ ደረጃ ዐቃቤ ሕግ በምርመራ ሥራ መግባት አይችልም፡፡ የእንግሊዝ፣ የሲንጋፖር እና የሆንግ ኮንግ ሕግን ስንመለከት የምንገኘው አካሄድም ከዚህ ብዙም የተለዬ አይደለም፡፡ ማለትም በምርመራ ወቅት በመርማሪው አካል ሥራ ውስጥ ዐቃቤ ሕግ ጣልቃ የመግባት አንዳች ሥልጣን የለውም፡፡

የኮንቲኔንታል ሎው የሕግ ሥርዓትን በሚከተሉ አገሮች ደግሞ በተቃራኒው የምርመራ ሥራ በዋናነት የዐቃቤ ሕግ ሥልጣንና ኃላፊነት ሲሆን ፖሊስ ምርመራ ለማካሄድ የሚችለው በዐቃቤ ሕግ ቁጥጥርና መመሪያ ሥራ ሆኖ ነው፡፡ በእነዚህ አገሮች ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ምርመራ እና በወንጀል ክስ ሥራ ላይ ዋናውን /ከፍተኛውን / ሚና ይጫወታል፡፡

በፈረንሳይ ማንኛውም ፖሊስ ምርመራ ማከናወን የማይችል ሲሆን ምርመራ ለማድረግ የሚችሉት Judicial police officers ተብለው የሚታወቁት ናቸው፡፡ እነዚህ የፍርድ ቤት (የፍትሕ) ፖሊሶች በወንጀል ጉዳይ ማናቸውም መረጃ ሲያገኙ ወድያውኑ ለዐቃቤ ሕግ እንዲያሳቁ የፈረንሳይ የሥነ ሥርዓት ይጠይቃል፡፡[14] ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ምርመራ በምን መልኩ ሊከናወን እንደሚገባ ለፖሊስን መመሪያ መስጠት እና በፖሊስ ላይ ቁጥጥር ማድረግ የሚችል ሲሆን ከዚህም አንጻር የምርመራው ባለቤት ዐቃቤ ሕግ ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በምርመራ ወቅት ዐቃቤ ሕግ ያለውን ተሳትፎ የሚመለከቱ ጉዳዮች በፈረንሳይ የሥነ ሥርዓት ሕግ ውስጥ በተለያዩ ድንጋጌዎች ላይ የምናገኝ ሲሆን ከዚህ አንጻር በተለይ አንቀጽ 41 እንደሚከተለው ይነበባል፡-

> “ The district prosecutor institutes or causes to be taken any step necessary for the discovery and prosecution of violations of the criminal law. To this end, he directs the

[14] የፈረንሳይ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 19

activity of the judicial police officers and agents within the area of jurisdiction of his court. The district prosecutor supervises police custody measures. He visits the places where persons are held whenever he considers this to be necessary and at least once every year; ….”

በማለት በምርመራ ላይ ለዐቃቤ ሕግ ሰፊ ሥልጣን ይሰጠዋል፡፡

ሌላው የፈረንሳይ የወንጀል ምርመራ አብይ ባህሪይ የሚገለፀው በወንጀል ስርዓቱ ውስጥ የወንጀል ምርመራ ሥራን የሚያከናውን የዳኝነት አካል ያለ መሆኑ ላይ ነው፡፡ Judge d’instruction ብለው የሚጠሩት Investigative judge ወይም መርማሪ ዳኛ ውስብስብና ከባድ በሆኑ ወንጀሎች ላይ ምርመራ የሚያከናውን ዳኛ ነው፡፡ የመርማሪ ዳኛ የወንጀል ተከሣሾችን አስቀርቦ የሚመረምር ሲሆን በጉዳዩ ምስክሮችን፣ተበዳዮችን ወዘተ አቅርቦ ቃላቸውን ይቀበላል፡፡ በምርመራ በተሳተፍበት የወንጀል ጉዳይ ላይ በመደበኛው የክስ መስማት (trial) ላይ መርማሪ ዳኛው በዳኝነት ተቀምጦ ሊያስችል አይችልም፡፡[15]

የመርማሪ ዳኛውንና የዐቃቤ ህግን ግንኙነት ዐቃቤ ህግ የያዘው ጉዳይ ከባድ ወንጀል ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ግድ ወደ መርማሪ ዳኞች ይዞ መምጣት አይጠበቅበትም፡፡ መርማሪ ዳኛ በዓቃቤ ህጉ ክትትል ሥር ይሆናል፡፡ የፍትህ ፖሊሶችም ቢሆኑ በራሳቸው ከመርማሪ ዳኛ ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት አይኖርም፡፡ መገናኘት ካስፈለጋቸው በአቃቤ ህግ በኩል ይሆናል፡፡ መርማሪ ዳኛውም ቢሆን እንዲሁ በራሡ ምንም የሚፈጽመው ነገር የሌለ ሲሆን ግዴታ የአቃቤ ህጉን ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፡፡

መርማሪ ዳኛው የሚኖረው ስልጣን ምርመራ በሚካሄድበት ወቅት ሰዎች ከ48 ሰዓት በላይ ተይዘው እንዲቆዩ ትዕዛዝ መስጠት፣ የስልክ ንግግሮችን መጥለፍ፣ ኤግዚቢቶችን መልቀቅ እና በጉዳዮች ውስጥ የሚፈጠሩ አዳዲስ ሂደቶችንም ሆነ መረጃዎችን መመርመር ናቸው፡፡ ሆኖም ግን በነኚህ ሁሉ ጉዳዮች ላይ ትዕዛዝ

[15] የፈረንሳይ የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 49

ከመሥጠቱ በፊት የአቃቤ ህጉን ሀሳብ መጠየቅ ይኖርበታል። አቃቤ ህግ ሀሳቡ ሳይጠየቅ መርማሪው ዳኛ ትዕዛዝ ተላልፎ ከሆነ ዐቃቤ ሕጉ ይግባኝ መጠየቅ ይችላል። በስተመጨረሻም ምርመራው ሲጠናቀቅ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ለመታየት ዝግጁ መሆኑንና አለመሆኑን መርማሪ ዳኛው ይወስናል።

ኢትዮጵያ የተከተለችውን መንገድ የትኛውን እንደሆነ ለመረዳት የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 9 እና 22/1/ ድንጋጌዎችን ስንመለከት የወንጀል ምርመራ ሥራ በዋናነት የፖሊስ ተግባር መሆኑን እንረዳለን። በተለይም በቁጥር 22/1/ ላይ "ፖሊስ የተሠራውን ወንጀል በሚያውቅበት ወይም በሚረዳበት ጊዜ ሁሉ በዚሁ ፍዕራፍ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ምርመራ ያደርጋል" ይላል። ከዚህ ድንጋጌ አቀራረብ የምንረዳው በኢትዮጵያ ሕግ የወንጀል ምርመራ እንዲያከናውን ሥልጣን የተሰጠው በዋናነት ለፖሊስ መሆኑን ነው። ይህ ሲባል ግን በልዩ ልዩ ሕጐች ከፖሊስ ውጭ ላሉ የተለያዩ አካላት በተለዩ ጉዳዮች ዙሪያ ምርመራ እንዲያደርጉ የተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው። ለምሣሌ ለልዩ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤትና ለፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን በተሰጣቸው ሥልጣንና ኃላፊነት ዙሪያ የወንጀል ምርመራ ለማድረግ እንዲችሉ የሚያስችል ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል።[16]

በሌላ በኩል ግን የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 8 ንዑስ ቁጥር 2 ላይ "የዐቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት ተግባሩን በሚፈጽምበት ጊዜ አስፈላጊ የሆነውን ትዕዛዝና መመሪያ ለፖሊስ እንዲተላለፍ ማድረግና ፖሊሶቹም በሕጉ መሠረት ግዴታቸውን መፈጸማቸውን ማረጋገጥ አለበት" ይላል። እንደዚሁም የኢ.ፌ.ዲ.ሪ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 471/98 አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 3 የፍትሕ ሚኒስቴር /በዐቃቤ ሕግነት ሥልጣኑ/ "በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ሥር የሚወድቅ ወንጀል ተፈፅሟል ብሎ ሲያምን ምርመራ እንዲደረግ ያዛል፣ በቂ ምክንያት ሲኖር የተጀመረ ምርመራ እንዲቆም ወይም ተጨማሪ ምርመራ እንዲከናወን ያደርጋል...." ይላል። የክልል ፍትሕ ቢሮዎች ማቋቋሚያ አዋጆችም ዐቃቤ

[16] የልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 22/84 አንቀጽ 6፣ የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 235/93 አንቀጽ 7(4)

ሕግ በወንጀል ምርመራ ውስጥ ያለውን ተሳትፎ በተመሳሳይ ሁኔታ ይደነግጋሉ። ለምሳሌ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት እንደገና ለማሻሻልና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 87/1997 አንቀጽ 16(23) "የወንጀል ምርመራ ክፍሎች ሥራቸውን በሕግ መሠርት ማከናወናቸውን ይቆጣጠራል፣ በዚህ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችንም ይሰማል፣ እንደአስፈላጊነቱም መመሪያ ይሰጣል በማለት ለክልል ፍትሕ ቢሮ(ለክልሉ ዐቃቤ ሕግ) ሥልጣንና ኃላፊነት የሚሰጠው ሲሆን እና የክልል ሦስት የሽግግር መስተዳድር ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መስሪያ ቤትን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 4/1985 አንቀጽ 11(2) ደግሞ የክልሉ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ " በክልሉ የወንጀል ምርመራ ክፍሎች በክልሉ ሕገ መንግሥትና በሌሎች ሕጎች መሠረት ሥራቸውን በሚገባ ማከናወናቸውን መቆጣጠር " ሥልጣንና ተግባሩ መሆኑን ይደነግጋል። ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ይዘት የምንረዳው አንደኛው ነገር ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ሕግ የምርመራ ሥራን በዋናነት ለፖሊስ የሰጠ ቢሆንም ዐቃቤ ሕግ በምርመራ ሥራው ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎችና ሁኔታዎች ጣልቃ እንዲገባ የሚፈቅድ መሆኑን ነው። የሚደገፈው አሠራርም በወንጀል ምርመራ ሥራ ላይ ዐቃቤ ሕግ እና ፖሊስ ተቀናጅተው መሥራታቸው ነው። ይህ አሠራር ከሚያስገኛቸው ጠቀሜታዎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- የወንጀል ምርመራ ሥራው ሕግ የተከተለና ጥራት ያለው እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፣
- አላስፈላጊ የተጨማሪ ምርመራ ትዕዛዞችንና በዐቃቤ ሕግ እና በፖሊስ መካከል የሚኖር የምርመራ መዝገብ ምልልስን ያስቀራል፣
- ዐቃቤ ሕግ በአጭር ጊዜ ውስጥ የወንጀል ክስ (charge) አዘጋጅቶ ለፍርድ ቤት ለማቅረብ እንዲችል አመቺ ሁኔታን ይፈጥርለታል።

5.2. <u>የዐቃቤ ሕግ የመክሰስ /ያለመክሰስ መብት</u>

በአንዳንድ በተለይም የኮመን ሎው የሕግ ሥርዓትን በሚከተል እንደ እንግሊዝ፣ አሜሪካ እና ካናዳ ያሉ አገሮች በወንጀል ለመክሰስ የሚያስችል በቂ ማስረጃ ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ የሕዝብን ጥቅም (Public interest) ግምት ውስጥ በማስገባት ተጠርጣሪውን

በወንጀል ያለመክሰስ ሥልጣን (discretionary power) አለው፡፡ እነዚህ አገራት (Discretionary principle)ን ተከትለው ለዐቃቤ ሕግ ሰፊ ሥልጣን የሰጡ አገሮች ናቸው፡፡

በአሜሪካ ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ጉዳይ ላይ ያለው ሥልጣን እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ በወንጀል ፍትሕ ሂደቱ ውስጥ የሞኖፖሊ ዓይነት ሥልጣን ያለው አካል ተደርጐ ነው የሚወሰደው፡፡ ተጠርጣሪውን በወንጀል ከስሶ ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል በቂ ማስረጃ ቢኖርም ዐቃቤ ሕጉ ያለመክሰስ ውሣኔ መስጠት ይችላል፡፡ በዚህ ውሣኔው ላይ ጣልቃ የሚገባበት ማንም አካል የለም፡፡

በሆንግ ኮንግ የወንጀል ክስ ፖሊሲ መሠረት ዐቃቤ ሕግ ተጠርጣሪውን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል ማስረጃ መኖሩን ካረጋገጠ በኋላ ክሱን ለመመስረት ጉዳዩ የሕዝብ ጥቅም ያለበት መሆኑን መወሰን አለበት፡፡ የሕዝብ ጥቅምን መሠረት በማድረግ የወንጀል ክስ ለመመስረት ወይም ላለመመስረት ግምት ውስጥ የሚገቡ ነገሮች እንደ ጉዳዮች ሁኔታ የሚለያይ ሲሆን በአጠቃላይ አነጋገር የተፈፀመው ወንጀል ከባድ በሚሆንበት ጊዜ የሕዝብ ጥቅም አለ ተብሎ የሚወሰድ ሲሆን ከዚህ ውጭ ግን በተለይም ከሚከተሉት የአንዱ መገኘት የሕዝብ ጥቅም የለም የሚያሰኝ ሁኔታ ተደርጐ ይወሰዳል፡፡[17]

- <u>**የተዘነጋ ጉዳይ መሆን**</u> - ወንጀሉ ከተፈፀመ በጣም ረዥም ጊዜ የሆነውና ህብረተሰቡ የዘነጋው ጉዳይ ከሆነ በዚያ ጉዳይ የወንጀል ክስ እንዲቀርብ የሕዝብ ጥቅም (Public interest) አይደለም ተብሎ ይወሰዳል፡፡ የተዘነጉ ጉዳዮች ክብደት ቢኖራቸውም አስፈላጊነታቸው አነስተኛ ነው ተብሎ ይገመታል፡፡

- <u>**የተጠርጣሪው ዕድሜ**</u> - ወንጀል ፈፃሚው በወጣትነት ዕድሜ ያለ ከሆነ በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ እንዲባል ማድረጉ በለጋ ዕድሜው ሊጠገን

[17] በፍትሕ ሚኒስቴር መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ለማምጣት ከተዘጋጀ የBPR ጥናት ጽሑፍ ላይ የተወሰደ(ያልታተመ)

የማይችል ጉዳት ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ የሚያስገድድ ሁኔታ በስተቀር በማስጠንቀቂያ ዐቃቤ ሕግ ሊያልፈው ይገባል፡፡

እንዲሁም ተጠርጣሪው ዕድሜው በጣም የገፋና እርጅና የያዘው ከሆነ ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ ከማቅረብ ሊታቀብ ወይም አግባብነቱን በቅጡ ሊያጤነው የሚገባ ይሆናል፡፡

- **<u>የተጠርጣሪው መፀፀት</u>-** የተፈፀመው ወንጀል ቀላል ዓይነት ወንጀል ከሆነና ተጠርጣሪው ወንጀሉን መፈፀሙን አምኖ በመፀፀት በወንጀሉ ምክንያት የደረሰውን ጉዳት ለማስተካከል በእርግጥ ከሞከረ ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ ለማቅረብ መድፈር የለበትም፡፡

- **<u>ክስ መመስረት የሚያስከትለው ጉዳት</u>-** በተጠርጣሪው ላይ ክስ በመመስረት እንዲቀጣ በማድረግ ከሚገኘውን ጥቅም ይልቅ በህብረተሰቡ ወይም በወንጀሉ ተጐጂ ላይ የሚያስከትለው ጉዳት በካናዳ (risk management) ይባላል፡፡ ከፍተኛ ከሆነ ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ መመስረቱ አይደገፍም፡፡ ለምሣሌ በባልና ሚስት መካከል የሚኖርን ግንኙነት (ትዳርን) አደጋ ውስጥ የሚጥል ከሆነ አንደኛው በሌላኛው በፈፀመው የወንጀል ተግባር ምክንያት ሊቀርብ ይገባ የነበረውን ክስ ከመመስረት መቆጠብ ዐቃቤ ሕግ ሊኖርበት ይችላል፡፡

- **ለፍትሕ አካላት ተጠርጣሪው ያደረገው ትብብር-** ተጠርጣሪው ሌሎች ተጠርጣሪዎች እና ወንጀሎች እንዲታወቁ እና እንዲያዙ ለማድረግ ለመተባበር ፈቃደኛ ሆኖ አስፈላጊውን እርዳታ ካደረገ ዐቃቤ ሕግ በተጠርጣሪው ላይ ከመመስረት መቆጠብ አለበት፡፡

- **<u>የተጐጂው ባህሪ</u>** - ወንጀሉ እንዲፈፀም ተጐጂው ባለው ባህሪ ምክንያት ከፍተኛውን አስተዋፅኦ ካደረገና የተፈፀመው ወንጀል ዓይነት ከሆነ ዐቃቤ ሕግ የወንጀል ክስ በተጠርጣሪው ላይ ለመመስረት መድፈር የለበትም፡፡

የኮንቲኔንታል ሎው የሕግ ሥርዓትን በሚከተሉ እንደ ጣሊያን እና ጀርመን ባሉ አገሮች ያለው ሁኔታ ደግሞ ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች የተለዬ ነው። ዐቃቤ ሕግ ተጠርጣሪውን በወንጀል ከሶ ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል በቂ ማስረጃ እስካለ ድረስ ክስ የመመስረት ግዴታ አለበት። የሕዝብ ጥቅምን ምክንያት በማድረግ በአንድ በወንጀል በተጠረጠረ ሰው ላይ ክስ አልመሰርትም ማለት አይችልም፣ ማለትም እንዲህ ዓይነት ሥልጣን አልተሰጠውም። እንዲህ ዓይነት ሥልጣን አልተሰጠውም። እነዚህ አገራት discretionary principleን አይከተሉም ወይም የሚከተሉት legality principleን ነው። ይህ በተለይ በጣሊያን አጥብቀው የሚከተሉት መርህ ነው።

በጀርመን ወንጀሉ ከባድ ዓይነት (felony case) ከሆነ ዐቃቤ ሕግ በቂ ማስረጃ እስካለ ድረስ የመክሰስ ግዴታ ያለበት ሲሆን ወንጀሉ ቀላል ዓይነት (minor case) ከሆነ ግን በቂ ማስረጃ ቢኖርም ዐቃቤ ሕግ እንደሁኔታው ያለመክሰስ ሥልጣን አለው።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ኢትዮጵያ የምትከተለውን መንገድ ስንመለከት ከወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 40 ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለው ተከሣሹን በወንጀል ጥፋተኛ ለማድረግ በቂ ማስረጃ እስካለ ድረስ ዐቃቤ ሕግ ክስ የመመስረት ግዴታ ያለበት መሆኑን ነው። በእርግጥ የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 42(1)(መ) የቀድሞው የፍርድ ሚኒስትር (በአሁኑ የፍትሕ ሚኒስትር) ለሕዝብ ጥቅም ሲባል የወንጀል ክስ እንዳይቀርብ ዐቃቤ ሕግን ማዘዝ እንደሚችል ይደነግጋል። ነገር ግን ይህ ድንጋጌ ከፍትሕ ሚኒስትሩ ውጭ ለሌላው ዐቃቤ ሕግ አግባብነት ያልነበረው ከመሆኑም ባሻገር ድንጋጌው በአዋጅ ቁጥር 11/1980 ተሽሯል። በእርግጥ አዋጅ ቁጥር 11/1980 በአዋጅ ቁጥር 39/1985፣ አዋጅ ቁጥር 39/1985 ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 74/1986 ተሽረዋል። ነገር ግን በመጨረሻ ሥራ ላይ ያለው አዋጅ ዐቃቤ ሕግ ለሕዝብ ጥቅም ሲል የወንጀል ክስ ከመመስረት ሊቆጠብ እንደሚችል እስካልፈቀደና ቀደም ሲል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ ተሰጥት የነበረውን ሥልጣን መልሶ እስካልሰጠው ድረስ የሥነ ሥርዓት ሕጉን ድንጋጌ የሻረው አዋጅ እራሱ በሌላ አዋጅ የተሻረ በመሆኑ ምክንያት ብቻ አንድ ጊዜ የተሻረ ሕግ

እንደገና ተፈፃሚ ሊሆን ስለማይችል[18] የወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 42(1) (መ) አሁንም ተፈፃሚነት የለውም ተብሎ ሊወሰድ ይችላል።

ስለዚህ ሕጋችን አሁን ባለበት ሁኔታ የወንጀል ክስ አቅርቦ ተከሣሹን ጥፋተኛ ለማሰኘት የሚያስችል በቂ ማስረጃ እስካለ ድረስ ዐቃቤ ሕግ የሕዝብን ጥቅም ግምት ውስጥ በማስገባት ክስ አልመሰርትም ማለት አይችልም።

5.3. <u>የእምነት ቃል ለመስጠት ስለ መደራደር</u>/Plea bargaining/

በሕግ ሙያ ዙሪያ የምንጠቀምባቸውን ቃላት እና ሀረጎች ወይም ፅንሰ ሀሳቦች ለመተርጎም ብዙ ጊዜ የምንጠቀምበት ብላክስ ሎው የሕግ መዝገበ ቃላት የእምነት ቃል ለመስጠት መደራደር /Plea bargaining/ የሚለውን ሐረግ እንደሚከተለው ተርጉሞታል።

> " plea bargain is a negotiated agreement between a prosecutor and a criminal defendant whereby the defendant pleads guilty to a lesser offense or to one of multiple charges in exchange for some concession by the prosecutor, usually a more lenient sentence or a dismissal of the other charges."[19]

በግርድፉ ሲተረጐምም የእምነት ቃል ለመስጠት መደራደር ማለት በድርድር የሚደረስበት ስምምነት ሲሆን በወንጀል የተከሰሰ ሰው ከተከሰሰበት ወንጀል ቀለል ያለ ወንጀል ወይም ከቀረቡበት የወንጀል ክሶች ውስጥ አንዱን ስለመፈፀሙና ጥፋተኛነቱን በማመን የእምነት ቃሉን ለመስጠት የሚስማማበት በምላሹ ደግሞ ዐቃቤ ሕጉ

[18] አንድን ሕግ የሻረ ሕግ ራሱ በሌላ ሕግ ከተሻረና የመጨረሻው ሕግ በመጀመሪያ በተሻረው ሕግ የተመለከተውን ጉዳይ በሚመለከት ምንም የሚለው ነገር ከሌለ ቀደም ብሎ የነበረው ሕግ ተፈጻሚ እንደሚሆን ሊወሰድ ይገባል በማለት የሚከራከሩ መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው።

[19] Black's Law Dictionary; 8th ed., 2004;p.1190

በአብዛኛው ቅጣቱ እንዲቀልለት ወይም በተከሳሹ ላይ ሊቀርቡ ከሚገባቸው የወንጀል ክሶች ውስጥ ከፊሎቹ ቀሪ እንዲሆኑ የሚስማማበት ሁኔታን የሚመለከት ነው፡፡

በዚህም መሠረት ተከሣሹ የእምነት ቃል የሚሰጥ ሲሆን በአንዣሩ ዐቃቤ ሕግ ደግሞ በተከሣሹ ላይ የሚያቀርበውን ክስ ከከባዱ ወደ ቀላል ለመቀየር ወይም የክሶቹን ቁጥር ለመቀነስ ወይም ደግሞ ከተከሣሹ ላይ የሚጣልበት ቅጣት እንዲቀነስለት ለማድረግ ስምምነት አድርገው ለፍርድ ቤት በማቅረብ ተፈፃሚ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

ይህ አሰራር የኮመን ሎው ሕግ ሥርዓትን በሚከተሉ አገሮች በሰፊው ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን በአጠቃላይ የወንጀል ጉዳዮች እስከ 90% (ዘጠና በመቶ) ድረስ በዚህ አሰራር የመጨረሻ እልባት እንደሚገኝ ይነገራል፡፡

በአብዛኛዎቹ የኮመን ሎው የሕግ ሥርዓትን ተከታይ ሀገሮች በዐቃቤ ሕግ እና በተከሣሽ መካከል በድርድር የሚደረገው ስምምነት ለፍርድ ቤት የሚቀርብ ሲሆን ፍርድ ቤቱም ተከሣሹ ጥፋተኛ መሆኑን በማመን ቃሉን ከመስጠቱ በፊት የስምምነቱ ዋና ሀሣብ የተረዳው መሆኑን፣ ጥፋተኛነቱን ያመነው በፈቃደኝነትና ያለ ተፅዕኖ መሆኑን፣ መረዳቱን፣ ጤንነቱ የተሟላ መሆኑን፣ በፍርድ ቤት ምስክሮች ቀርበው መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ ወ.ዘ.ተ. መብቶቹን ላለመጠቀም የተስማማ ስለመሆኑ መረዳቱን፣ ለክሱ መንስኤ የሆኑ ሥረ ነገሮችን ተከሳሹ የተረዳቸው ስለመሆኑ፣ወ.ዘ.ተ. ያረጋግጣል፡፡

የእምነት ቃል ከተከሣሽ ለማግኘት በዐቃቤ ሕግ እና በተከሣሽ መካከል በሚደረግ ድርድር የሚገኝ ስምምነት የራሱ የሆነ ጠቀሜታዎች እና ጉዳቶች አሉት፡፡ እነዚህ በአሰራሩ ዙሪያ የሚታዩ ወይም የሚነሱ ጠቀሜታዎች (ድጋፎች) እና ጉዳቶች (ነቀፌታዎች) ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ ተመልክተዋል፡፡

ጠቀሜታዎቹ (ድጋፎቹ)	ጉዳቶቹ (ነቀፊታዎቹ)
1. የፍርድ ሂደቱን በማሳጠር ወጪን፣ ጊዜንና ውጣ ውረድን ይቀንሣል፣ 2. የወንጀል ጉዳዮች በፍጥነት ውሣኔ እንዲያገኙ በማስቻል የፋይል ክምችትን ይቀንሣል፣ 3. መደበኛ የሆነው የክስ መስማት ሂደት (Trial) ቢካሄድ ኖሮ ተከሣሹ ጥፋተኛ ሆኖ ሊገኝ ወይም ላይገኝ የሚችል በመሆኑ ስምምነቱ ይህን አደጋ (risk) ወይም እርግጠኛ አለመሆን (Uncertainty) ያስቀራል፣ 4. ለሕግ አስከባሪ አካላት ሌሎች ወንጀሎችን ለመድረስና ወንጀለኞችን ለመያዝ ድጋፍ /መረጃ/ ይሰጣቸዋል፡፡ 5. ተከሣሹ የእምነት ቃሉን ለመስጠት እንዲደራደር ምክንያት የሆኑትን ጥቅሞች እንዲያገኝ ያስችለዋል ማለትም የሚቀርብበት ክስ ከከባድ ወደ ቀላል ይቀየርለታል፣ ወይም የሚቀርብበት ክስ ቁጥር ይቀንስለታል፣ ወይም የሚጣልበት ቅጣት ይቀንስለታል፡፡	1. ንፁህ የሆነ ሰው ሊቀጣ ይችላል ማለትም በመደበኛው የክስ መስማት ሂደት (Trial) ውጤት ላይ ባለመተማመን risk ላለመውሰድ ሲባል ንፁህ ሰዎች ጥፋተኛ ነኝ በማለት ቀለል ያለ ቅጣት ለመቀጣት ሊመርጡ ይችላሉ፡፡ 2. አሰራሩ ድርድሩን የተቀበለ ተከሣሽ ያነሰ ቅጣት አንዲቀጣ ድርድሩን ያልተቀበለ ተከሣሽ ደግሞ ሕገ መንግሥታዊ መብቱን በመጠቀሙ የበለጠ ቅጣት እንዲቀጣ የሚያደርግ በመሆኑ ተገቢነት የለውም፡፡ 3. ብዙ ጊዜ ስምምነቱ የወንጀል ድርጊቱን ተጐጂ (የግል ተበዳይን) ግምት ውስጥ አያስገባም፤ ማለትም የግል ተበዳዩን ፍትህ የማግኘት መብት ያላገናዘበ ነው፡፡ 4. ሕብረተሰሱ (ለሕግ) ማክበር ያለውን ቦታ ዝቅ የማድረግ ውጤት ሊኖረው ይችላል፡፡ ከባድ ወንጀል የፈፀመ በቀላል ወንጀል ተከሶ እንዲቀጣ ከተደረገ፣ ብዙ ወንጀሎችን የፈፀመ በተወሰኑ ወንጀሎች ብቻ የሚጠየቅ ከሆነ እንዲህ ዓይነት አሰራሮች ሕግ ያለማክበር ሁኔታን ሊያበረታቱ ይችላሉ፡፡ 5. ለሙስና ለብልሹ አሰራር መንገድ ሊከፍት ይችላል፡፡ ድርድሩ የሚደረገው በዐቃቤ ሕግና በተከሣሹ (በጠበቃው) መካከል ሲሆን ብዙ ጊዜ በምስጢር የሚከናወን ነው፡፡ እንዲሁም አሰራሩ ግልፅነት የጐደለው ነው፡፡ 6. ተከሣሹን ወደ ድርድር ለማምጣት ሲባል ዐቃቤ ሕግ አላግባብ ተከሣሹን የማያስከስሰውን ሁሉ ለማስፈራራት ሲል ክስ አንዲያቀርብ ይገፋፋዋል (Overcharging) ፣

ተከሣሹ የእምነት ቃል እንዲሰጥ ለማድረግ መደራደርን በተመለከተ ኢትዮጵያ የምትከተለውን መንገድ ስንመለከት ይህ አሰራር በኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ውስጥ በግልፅ ተካትቶ አናገኘውም፡፡ በእርግጥ በአዲሱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 82(1)(ሠ) ላይ እንደተመለከተው ተከሳሹ የፈፀመውን ጥፋት በመገንዘብ ራሱን ለፍትሕ አካላት ካቀረበ ወይም ተከስሶ ፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ በክስ ማመልከቻው ላይ የተመለከተውን የወንጀል ዝርዝር በሙሉ ያመነ እንደሆነ ይህ ተግባሩ የቅጣት ማቅለያ ተደርጐ ሊወሰድለት ይችላል፡፡ ይህ ማለት ግን በተከሣሽና በዐቃቤ ሕግ ወይም በተከሣሽ እና በፍርድ ቤት መካከል ተከሣሹ የእምነት ቃሉን እንዲሰጥ ለማድረግ የሚደረግ ድርድር ይኖራል ማለት አይደለም፡፡

6. ዐቃብያነ ሕግ በወንጀል የፍትሕ ስርዓት ውስጥ ያላቸው ሚና

በ1954 ዓ.ም የወጣው የኢትዬጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ጉዳይ ከመከላከል እስከ መጨረሻው ደረጃ ማለትም ተጠርጣሪን በበቂ ማስረጃ እስከ ማስቀጣት ባለው ሂደት ሊጫወት የሚገባውን ወሳኝ ሚና በዝርዝር አስቀምጧል፡፡ ከሥነ ሥርዓት ሕጉ በተጨማሪ ዐቃብያነ ሕግ በወንጀል የፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ስለሚኖራቸው ሚና አንዳንድ ጉዳዮችን በዐቃብያነ መስሪያ ቤቶች (የፍትሕ ሚኒስቴርና የፍትሕ ቢሮዎች) እንዲሁም በሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽኖች እና በልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጆች ተመልክተው እናገኛቸዋለን፡፡

ለአንድ የወንጀል ፍትሕ አስተዳደር ውጤታማነት በተለይ የሶስቱ ዋነኛ ተዋንያን ማለትም የፖሊስ፣ ዐቃቤ ሕግ እና የፍርድ ቤት ፍትሕን ማዕከል ያደረገ የጋራና የተናጠል እንቅስቃሴ ወሳኝ መሆኑ የማያጠያይቅ ቢሆንም በተለይ ዐቃቤ ሕግ

የመንግስትና የህብረተሰቡ፣ የግለሰብ ተጎጂዎች ብሎም የተጠርጣሪዎች መብትና ጥቅሞች የሚከበሩበት ሁኔታ እንዲፈጠር የሚጫወተው ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው።

6.1. በወንጀል ምርመራ ስራ ላይ የዐቃቤ ሕግ ተሳትፎ

ዜጐች በወንጀል ስራ በማናቸውም መብቶቻቸው እና ጥቅሞቻቸው ላይ ጉዳት ቢደርስ መብቶቻቸውን ለማስከበር የሚችሉበትና አለኝታ የሚሆን ውጤታማ የወንጀል ምርመራ ስራ ሊኖር ይገባል ።

መንግስት ይህን ተግባር የሚያከናውነው በዋነኛነት በመርማሪ ፖሊስ ወይም ለተመሣሣይ አላማ በተቋቋመ ሌላ አካል ሊሆን ቢችልም ዐቃቤ ሕግ በማናቸውም አካል የሚደረገው ምርመራ የተፈጸመውን ወንጀልና ተጠርጣሪውን ለይቶ በማውጣት ለፍርድ ሊያበቃ በሚችል አቅጣጫ እየተከናወነ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል። በሌላ አነጋገር የሚደረገው ምርመራ ከማናቸውም ዓይነት ተጽዕኖ የፀዳና እና አንዱን ወገን ጠቅሞ ሌላውን ለመጉዳት ያልታቀደ ወይም ለይምሰል የማድረግ ሳይሆን እውነተኛ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል ።

በ1949 ዓ.ም በታወጀው የኢትዮጵያ ወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 8/2/ እና 9 ላይ በወንጀል ምርመራ ስራ ዐቃቤ ሕግ ለፖሊስ አስፈላጊውን መመሪያ ሊሰጥ እንደሚችልና ፖሊስም ስራውን በሕግ መሰረት ማከናወኑን ማረጋገጥ እንደሚጠበቅበት ተመልክቷል ። ከዚህ መሠረታዊ ሕግ በኋላ በተከታታይ የወጡ ሌሎች ሕጐችም ይህንኑ የሚያጠናክሩ ናቸው።[20] ይሁን እንጂ በወንጀል ምርመራ ስራ ረገድ በፖሊስ እና በዐቃቤ ሕግ መካከል በተግባር ያለውን ግንኙነት በምንመለከትበት ወቅት ዐቃቤ ሕግ በሕግ የሚጠበቅበትን የመሪነት ሚና በመጫወት የተጣለበትን ኃላፊነት እየተወጣ ነው ለማለት አያስደፍርም ።

በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ድርጊት ተጠርጥረው ስለሚያዙ ሰዎች ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች አቤቱታ ሲቀርብለት ካልሆነ በቀር ተጠርጥሮ የተያዘው ሰው

[20] ለምሳሌ አዋጅ ቁጥር 11/80ትን እና 471/98 አንቀጽ 23(3)ትን መመልከት ይቻላል።

በእርግጥም ለተፈጸመው ወንጀል ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው መሆኑን በራሱ ሊከታተል የሚያስችለው ስልት ያለው ሆኖ አይታይም፡፡ በዚህም ምክንያት ሰዎች በማያውቁት ጉዳት ታስረው የሚንገላቱበት አጋጣሚ የመኖሩን ያህል ከፍተኛ ወንጀል ፈጽመው ሳይደረስባቸው የሚቀሩ እንደዚሁ በቁጥር ትንሽ አይደለም ፡፡ በተጠርጣሪዎች ወይም በምስክሮች ቃል አቀባበል ወይም በሌሎች ማስረጃዎች አሰባሰብ ረገድም ዐቃቤ ሕግ የሚጠበቅበትን የመሪነት ሚና በመጫወት የምርመራ ስራ ውጤታማ እንዲሆን እያገዘ ነው ለማለት አይቻልም ፡፡ በዚህም ምክንያት ዛሬ የምርመራ አካላት በራሳቸው ጊዜና አቅም አስናውነው ለዐቃቤ ሕግ ከሚሉኳቸው የምርመራ መዛግብት ውስጥ ተጠርጣሪውን ያልለዩ ወይም በተጠርጣሪነት የቀረበው ሰው ወንጀሉን ለመፈጸሙ የሚያረጋገጥ በቂ ማስረጃ ባለመሰብሰቡ የአያስከስስም ውሣኔ የሚሰጥባቸው መዛግብት ቁጥር ቀላል አይደለም ፡፡

በፖ/ሊስ ክፍል አላግባብ ታሰርኩ የሚል አቤቱታ ከተከሳሽ ሲቀርብለት ተከሣሹን የያዘው ያጠናከረውን የምርመራ መዝገብ ተከሣሽ ወንጀሉን ያልፈጸመ መሆኑን ሲረጋገጥ የምርመራ መዝገቡን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 42(1)(ሀ) መሠረት ዘግቶ ተከሣሽ እንዲለቀቅ ትዕዛዝ ይሰጣል ፡፡

እንዲሁም የተያዙ ሰዎች በሕገ መንግስቱ በተደነገገው መሠረት ወደ ፍርድ ቤት እየቀረቡ መሆኑና በአገሪቱ የወንጀል ሕግ በወንጀል በሚያስጠይቅ ጉዳይ ብቻ እንጂ በሌላ ጉዳይ አለመታሰራቸውን በመከታተል አያያዙ ሕገ ወጥ ሆኖ ከተገኘ የተያዙ ሰዎች እንዲለቀቁ ትዕዛዝ በመስጠትና ለዚህም ተጠያቂ በሆኑት ላይ ሕጋዊ እርምጃ በመውሰድ /እንዲወሰድ/ በማድረግ ዐቃቤ ሕግ የተጣለበትን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል፡፡

ከዚህ አንጻር አሁን በአገሪቷ ያለውን የዐቃቤ ሕግ ሁኔታ በምንመለከትበት ወቅት ከፌዴራሉ ዐቃቤ ሕግ ይልቅ የክልል ዐቃብያነ ሕግ የተመቻቸ የሕግ ሁኔታ እንዳላቸው እንረዳለን ፡፡ በዚህም መሠረት የክልል ፍትሕ ቢሮዎች በፖ/ሊስ ጣቢያና በማረሚያ ቤቶች ያሉ ሰዎችን አያያዝ ሁኔታ ለመከታተልና ለመቆጣጠር የሚያስችል

ግልጽ ስልጣን በማቋቋሚያ ሕጐቻቸው የተሰጣቸው ሲሆን[21] የፌዴራል አስፈጻሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 471/98 አንቀጽ 23ት ግን ይህንን አይነቱን ስልጣን ለፌዴራሉ ዐቃቤ ሕግ በግልጽ አይሰጥም ። በዚህም ምክንያት የፌዴራሉ ዐቃቤ ሕግ በአዲስ አበባ እና በድሬድዋ ከተሞች በሚገኙ ፖሊስ ጣቢያዎችና ማረሚያ ቤቶች የታቀደ ወይም ያልታቀደ ጉብኝት በማድረግ ሰዎች በአግባብ የተያዙ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ አጥጋቢ እንቅስቃሴ አድርጓል ለማለት አይቻልም ።

በአጠቃላይ ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ስራን በሚሰራበት ወቅት የሙያ ነፃነቱ የተጠበቀ መሆኑ የሚታመን ቢሆንም ተግባሩን በሕግ መሠረት እያከናወነ ለመሆኑ መከታተልና ማረጋገጥ የዐቃቤ ሕግ የምንግዜም ኃላፊነት መሆኑ ግን ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው ።

6.2. ከምርመራ በኋላ እና ከክስ በፊት የዐቃቤ ሕግ ሚና

ዐቃቤ ሕግ ምርመራው ተጣርቶ በደረሰው ጊዜ በምርመራ መዝገቡ ላይ የአያስከስስም ወይም የይዘጋ ውሣኔ መስጠት ፤ ተጨማሪ ምርመራ እንዲደረግ ፖሊስን መጠየቅ ፣ ቀዳሚ ምርመራ እንዲደረግ የማድረግ ወይም ክስ መመስረት ይችላል ።

ማንኛውም ዐቃቤ ሕግ በተጠርጣሪ ላይ የቀረበው ማስረጃ ሊያስቀጣ የማይችል ወይም በቂ ባልሆነ ጊዜ ወይም ተከሣሹን ማግኘት በማይቻልበት ጊዜ እና ጉዳዩን በሌለበት ማየት የማይቻል በሆነ ጊዜ ወይም ለተፈጸመው ወንጀል ምህረት የተሰጠ ወይም ይቅርታ የተደረገ በሆነ ጊዜ ወይም ክሱ በይርጋ የታገደ በሆነ ጊዜ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 42/1/ መሠረት የአያስከስስም ውሣኔ እንዲሰጥ ስልጣን ተሰጥቶታል ።

እንደዚሁም ተከሣሹ እድሜው ከዘጠኝ ዓመት በታች ከሆነ ወይም ከሞተ ወይም በአለም አቀፍ ሕግ መሰረት ያለመከሰስ መብት ያለው ከሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ

[21] ለምሳሌ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት እንደገና ለማሻሻልና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 87/1997 አንቀጽ 16(26) እና የክልል ሦስት የሽግግር መስተዳድር ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መስሪያ ቤትን ለማቋቋም የወጣውን አዋጅ ቁጥር 4/1985 አንቀጽ 11(4) ድንጋጌዎችን ይመለከቷል።

ስርዓት ሕግ ቁጥር 39 መሠረት ክስ ባለመመስረት መዝገቡን የመዝጋት ኃላፊነት አለበት ። በተጨማሪም ዐቃቤ ሕግ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 54(6) መሠረት ፍቃድ ካልተገኘ በስተቀር ያለመከሰስ መብት ያላቸው ሰዎች ተከሰው ከቀረቡ ክሱን የመዝግት ኃላፊነት አለበት ።

በተጨማሪም በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 130 መሰረት በተከሰሱበት ወንጀል በሌላ ፍርድ ቤት ክስ ተጀምሮ በቀጠሮ ላይ ያሉ ሰዎች ላይ ወይም በቀረበባቸው ክስ ቀደም ብሎ ተከሰው ነጻ የተለቀቁ ወይም የጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጣቸውና በሕገ መንግስቱና በወንጀል ሕጉ በተደነገገው መሠረት በአንድ ወንጀል ሁለት ጊዜ ሊከሰሱ በማይችሉ ሰዎች ላይ የወንጀል ምርመራ ተደርጎ ሲቀርብለት ዐቃቤ ሕግ ክስ መመስረት አይኖርበትም።

የምርመራ መዝገብ ተሟልቶ ባልተገኘ ጊዜ ያልተሟሉ ነጥቦችን በመለየት መርመሪው ፖሊስ አጣርቶ እንዲያመጣ ዐቃቤ ሕግ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 38(ሐ) መሠረት ትዕዛዝ የመስጠት ኃላፊነት አለበት። በዚህም መሰረት የምርመራ መዝገቡን ዐቃቤ ሕግ ሲመረምር የተሳሳተ ነገር ካለ እንዲስተካከል፣ ቃላቸውን የሰጡ ምስክሮች ሊጠየቁ የሚገባቸው ነገር ሳይመዘገብ ቀርቶ እንደሆነ ወይም ምስክሮች በሰጡት ቃል ውስጥ የተጠቀሱና በምስክርነት ጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉ ምስክሮች አልተጠየቁ እንደሆነ ቃላቸውን እንዲሰጡ ለማድረግ ወይም በምስክሮች የተጠቀሰ ሰነድ ወይም ሌላ ማስረጃ በመርማሪው ሳይታይ ቀርቶ እንደሆነ እንዲሟላ ለማድረግ በመሳሰሉት ምክንያቶች ዐቃቤ ሕግ ተጨማሪ ምርመራ ወይም ማስተካከያ እንዲደረግ መመሪያ መስጠት ይችላል። የሚሰጠው መመሪያ ወይም ትእዛዝ ደግሞ ወቅታዊና ተጨባጭ ሁኔታዎችን የተከተለ፣ ግልፅና በታቻለ መጠን የማያዳግም(exhaustive) መሆን አለበት።[22]

ከባድ የግፍ አገዳደል ወይም ከባድ የወንበዴነት ወንጀል ተፈጽሟል ተብሎ ምርመራ ተጣርቶ በሚቀርብበት ጊዜ ከከፍተኛው ፍርድ ቤት ፈቃድ ካልተገኘ በቀር ዐቃቤ ሕግ የግድ የቀዳሚ ምርመራ እንዲደረግ ማድረግ ያለበት ሲሆን በሌሎች

[22] መዝገበ ምትኬ፣ ስለ ዐቃቤ ሕግ አሰራር አንዳንድ ነጥቦች፣ አዲስ አበባ፣1980(ያልታተመ)

በከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር በሚወድቁ የወንጀል ጉዳዮች ላይ ግን እንደአስፈላጊነቱ የቀዳሚ ምርመራ እንዲደረግ ማድረግ ይችልላል ።

የፖሊስ የምርመራ መዝገቡን ያጠናው ዐቃቤ ሕግ ሊያስቀጣ የሚችል በቂ ማስረጃ ሲኖርና ያስከስሳል ብሎ ሲያምን ማስረጃና ሕጉን በማገናዘብ በወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕጉ ላይ ያሉትን የክስ ማመልከቻ ፎርሞችን በመከተል ክስ አዘጋጅቶ ማቅረብ አለበት።

6.3. <u>የወንጀል ክስ በማቅረብ ወቅት የዐቃቤ ሕግ ሚና</u>

ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ጉዳይ ክስ ለመቀጠል አስፈላጊ የሆኑት በወንጀል ሕጉና በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕጉ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች መሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት። እነዚህም ሁኔታዎች ወንጀሉ በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚያስከስስ የሆነ እንደሆነ የግል ተበዳዩ ምርመራ እንዲጣራና ክስ እንዲቀርብ ፈቃዱን የሰጠ መሆን አለመሆኑን፣ ተከሳሹ በዐቃቤ ሕግ አሁን በመመርመርና በመታየት ላይ ባለው የወንጀል ጉዳይ ከዚህ በፊት ተከስሶ የተቀጣ ወይም ነጻ የተለቀቀ መሆን አለመሆኑን፣ የወንጀል ክሱን ለማቅረብ ወይም ቅጣቱን ለማስፈፀም የሚያስፈልገው የጊዜ ገደብ ያለፈ ወይም ክሱ በይርጋ የተቋረጠ መሆን አለመሆኑን[23] እና መሰል ጉዳዮችን የማጣራትና የወንጀል ሥነ ሥርዓት ሕጉ በሚጠይቀው መሠረት የወንጀል ክሱን አዘጋጅቶ ማቅረብ አለበት።

ይህን ተግባሩን በአግባቡ መወጣት አለመወጣቱ በወንጀል ፍትሕ አስተዳደሩ ውስጥ ከፍተኛ እንድምታ ያለው ሲሆን በተለይም የተጠርጣሪውን መብት በማጣበብ ረገድ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል መሆኑ ግልፅ ጉዳይ ነው።

[23] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 216(2) አንድ የወንጀል ክስ በይርጋ ስለመታገዱና ክሱን ለመቀበል የማይገባ ስለመሆኑ ተከሳሹ ባያመለክትም ዐቃቤ ሕግ ወይም ፍርድ ቤት በማናቸውም ጊዜ ማንሳት እንዳለበት ይደነግጋል።

6.4. በወንጀል ሙግት /ክርክር/ ወቅት የዐቃቤ ሕግ ተሳትፎ

ዐቃቤ ሕግ ከፖሊስ የቀረበለትን የምርመራ መዝገብ አጥንቶ/ መርምሮ / ተከሣሹ የተጠረጠረበትን ወንጀል ፈጽሟል የሚል መደምደሚያ ላይ ሲደርስ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕጉ በሚያዘው መሠረት የወንጀል ክስ ማመልከቻውን አዘጋጅቶ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ያቀርባል ።

ክስ ከቀረበ በኋላ ፍርድ ቤት በየቀነ ቀጠሮ በመቅረብ ክርክር የሚያደርግ ሲሆን ይህ የስራ ሂደት ብዙ እንቅስቃሴዎችን የሚያካትት በወንጀል የፍትሕ ስርዓት ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያለው ስራ ነው። የስራው የመጨረሻ ውጤትም ወንጀል ስለመፈጸማቸው በማስረጃ የተረጋገጠባቸው ወንጀለኞች ጥፋተኛነታቸው ተረጋግጦ ለጥፋታቸው ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት እንዲጣልባቸው ማድረግ ሲሆን በዚህ ሂደት ውስጥ ዐቃቤ ሕግ የሚፈልግበትን ተሳትፎ ካላደረገ በስተቀር የወንጀል ፍትሕ ስርዓቱ ውጤታማ ሊሆን የሚችል አይደለም ።

ፍርድ ቤት የተከሣሹን በዋስ የመልቀቅ መብት ጥያቄ የሚወስነው ሕግን መሠረት አድርጎ ቢሆንም በጉዳዩ ላይ ዐቃቤ ሕግ የሚሰጠው አስተያየት ከፍተኛ ቦታ አለው። በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ በዋስትና ጥያቄው ላይ ያለውን አስተያየት ሕግንና አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች ብቻ መነሻ በማድረግ ያለ አድልዎ መግለፅ አለበት።

ሌላው በሙግት ወቅት የሚታየው ጉዳይ ለክርክሩ የሚቀርብ ማስረጃን የሚመለከት ነው። ዐቃቤ ሕግ ትክክለኛ ማስረጃን በትክክለኛ መንገድ እና በትክክለኛው ወቅት ማቅረብ አለበት። ለምሳሌ በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 138(1) ላይ እንደተመለከተው “ሕጉ በግልፅ ካልፈቀደ በቀር በፍርድ ጥፋተኝነቱ ከመታወቁ በፊት ተከሳሹ ከዚህ በፊት ተከሶ የጥፋተኛነት ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑ...” መገለፅ የሌለበት በመሆኑ ዐቃቤ ሕግ ማስረጃ በሚያቀርብበት ወቅት እንዲህ ዓይነት ክልከላዎችን ግምት ውስጥ ማስገባትና ማስረጃውን ወቅቱን ጠብቆ በተከሳሹ ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ ማቅረብ ይጠበቅበታል። ወቅቱን ሳይጠብቅ እንዲህ

ዓይነት ማስረጃዎችን ለችሎት ቢያቀርብ ፍርድ ቤቱ ሕጉን ተከትሎ እንደማይቀበለው ሊገመት ቢችልም ሕጉ ለመከላከል የሚፈልገው ተከሳሹ ከዚህ በፊት በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ተገኝቶ የነበረ ስለመሆኑ በፍርድ ቤቱ በመታወቁ አሁን የቀረበውን ክስም ፈጽሞታል ተብሎ እንዳይገመትና ንፁህ ሆኖ የመገመት መብቱን እንዳይነካ ለመጠበቅ ቢሆንም ዳኛው የቀረበውን ማስረጃ ወቅቱን ሳይጠብቅ መቅረቡን በማየት ውድቅ ሲያደርገው በዚያው ግን ተከሳሹ ከአሁን በፊት ወንጀል ፈጽሞ ጥፋተኛ መባሉን የሚረዳ በመሆኑ የሕጉ ዓላማ እንዳይሳካ የማድረግ ውጤት ይኖረዋል፡፡

ዐቃቤ ሕግ በተከሣሹ ላይ የወንጀል ክሱንም ሆነ ሌላ ማናቸውም ጉዳይ ለፍርድ ቤት ሲያቀርብ "በትክክል ያለ አድልዎ" ማቅረብ አለበት፡፡[24] ሚዛናዊ በሆነ መንገድ አቅርቦ ፍትሕ እንዲበየን መጠየቅ ይኖርበታል፡፡ ለዚህም ዐቃቤ ሕግ ምንጊዜም ለፍትሕ የቆመ መሆን አለበት፡፡

የሙግት ስራው እንደአስፈላጊነቱ በይግባኝ እና በሰበር ደረጃ የሚቀጥል ሲሆን ይህም የሚሆነው ተከሣሹ አላግባብ ከቀረበበት ክስ በነፃ ሲለቀቅ ወይም ጥፋተኛ የተባለው አግባብነት በሌለው የወንጀል ድንጋጌ ወይም ጥፋተኛ ከተባለበት ወንጀል የሚገባውን ተመጣጣኝ ቅጣት ሳይጣልበት ሲቀር ወይም ደግሞ የፍርድ ቤቱ ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት መሆኑን ዐቃቤ ሕግ በሚያምነበት ጊዜ ነው፡፡ በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ የይግባኝ አቤቱታ እንዲያቀርብ በሕግ ወይም በፍሬ ነገር የተደገፈ መሠረት ያላቸው ምክንያቶች መኖር አለባቸው፡፡ የሰበር አቤቱታን ለማቅረብም እንደዚሁ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መኖሩን የሚያሳዩ ሁኔታዎች በፍርድ ቤቱ ወይም ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ውስጥ መኖር አለበት፡፡

6.5. ከፍርድ በኋላ የዐቃቤ ሕግ ተሳትፎ

በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው በፍርድ ቤት ተገቢው ቅጣት እና/ወይም የጥንቃቄ እርምጃ የሚወሰንበት ሲሆን ዐቃቤ ሕግ ፍርዱ ከተሰጠ በኋላ ያለው ሚና

[24] የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 136(1)

ምንድነው የሚለውን በተመለከተ በ1980 ዓ.ም የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤትን ለማቋቋም ወጥቶ በነበረው አዋጅ ቁጥር 11/80 አንቀፅ 14/7/ ዐቃቤ ሕግ፡-

> " በእስረኞች ላይ የሚፈፀሙ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ሕግንና የእስር ቤት ደንቦችን የተከተሉ መሆናቸውንና እስረኞችም የሚገባቸውን እንክብካቤ ማግኘታቸውን መቆጣጠር፣ ጉድለት ባጋጠመው ጊዜም እንዲስተካከል ማድረግ አለበት"

የሚል ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶት ነበር፡፡

ይህ አዋጅ የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት የማዕከላዊ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 39/85 ሲሻር በሻረው አዋጅ አንቀጽ 12 ላይ ተመሳሳይ ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም አሁን የፌዴራል ዐቃቤ ሕግን በተመለከተ ተፈጻሚነት ባለው አዋጅ ቁጥር 74/86ትም ሆነ የፍትሕ ሚኒስቴርን ሥልጣንና ተግባር በሚወስነው አዋጅ ቁጥር 471/98 አንቀጽ 23 የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ ከፍርድ በኋላ ያለውን ሚና በሚመለከት ምንም የሚሉት ነገር የለም፡፡

ስለዚህም የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ በወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎችችን ከስሶ አግባብነት ያላቸውን ማስረጃዎች አቅርቦና ተገቢውን ክርክር አድርጎ ካስፈረደ በኋላ በአጥፊዎች ላይ የተጣለው ቅጣት ተፈጻሚ ስለመሆኑና አፈጻጸሙ ሕግ በሚያዘው መሠረት ስለመሆኑ ተገቢውን ክትትል ለማድረግና እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችለው በግልፅ በሕግ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር የለውም፡፡

ከዚህ አንጻር አሁን ከፌዴራሉ ዐቃቤ ሕግ ይልቅ የክልል ዐቃብያነ ሕግ የተመቻቸ የሕግ ሁኔታ እንዳላቸው እንረዳለን ፡፡ ለምሳሌ የኦሮሚያና የአማራ ክልሎች ዐቃብያነ ሕግን ብንመለከት በክልሎቹ ውስጥ በሚገኙ ማረሚያ ቤቶች (እስር ቤቶች) በመገኘት በወንጀል ጥፋተኛ ሆነው ተገኝተው እስራት የተፈረደባቸው ሰዎች በምን ዓይነት ሁኔታ ቅጣታቸውን እየፈፀሙ እንደሚገኙ የመቆጣጠርና አስፈላጊውን መመሪያ የመስጠት ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቷቸው እናገኛቸዋለን፡፡ በተለይም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት እንደገና ለማሻሻልና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ ቁጥር 87/1997 አንቀጽ

16(26)ትን ስንመለከት የክልሉ ፍትሕ ቢሮ (ዐቃቤ ሕግ) "የእስረኞችና የተያዙ ወይም የታሰሩ ሰዎች አስተዳደር በሕግና በሥርዓት መሆኑን..." የመቆጣጠርና አስፈላጊውን መመሪያ የመስጠት ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

በአጠቃላይ ዐቃቤ ሕግ ያለበትን ሕግ የመጠበቅና የማስከበር ኃላፊነት ስንመለከት የተጣሰውን ሕግ ወክሎ ከከሰሰና ካስፈረደ በኋላ በዛው "ሕግ የመጠበቁ" ሥራ ተጠናቋል ብሎ ማቆም ያለበት አይመስልም። የተፈረደበት ሰው የተወሰነበት ፍርድ የተፈፀመበት ስለመሆኑና አፈጻጸሙ ሕግን የተከተለ ስለመሆኑ መከታተልና ማረጋገጥ አለበት።

7. <u>ዐቃብያነ ሕግ በፍትሐብሔር የፍትሕ ስርዓት ውስጥ ያላቸው ሚና</u>

በኮመን ሎው የሕግ ሥርዓት የዐቃቤ ሕግ ዋነኛ የሥራ ድርሻ የወንጀል ጉዳዮችን መከታተል ሲሆን ይህ ሊሆን የበቃውም የማህበረሰቡ የጋራ መብትና ጥቅም ሊነካ (ሊጠቃ) የሚችለው በወንጀለኞች ብቻ በመሆኑ ወንጀለኞችን ተከታትሎ በወንጀል እንዲጠየቁ በማድረግ የማህበረሰቡን መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ይቻላል በሚል እምነት ይመስላል።[25] በተነጻጻሪ የሲቪል ሎው የሕግ ሥርዓትን ስንመለከት ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ጉዳይ ዙሪያ ካለው የሥራ ድርሻ በተጨማሪ በፍትሐብሔርም ሰፊ የሥራ ድርሻ ያለው ሆኖ እናገኘዋለን። እንደ ሲቪል ሎው የሕግ ሥርዓት ተከታይ አገሮች ሁሉ በኢትዮጵያም የዐቃቤ ሕግ የሥራ ድርሻ የወንጀል ጉዳዮችን በመከታተል ዙሪያ ብቻ የተገደበ አይደለም።

በአገራችን የፍትሐብሔር ጉዳዮችን አስመልክቶ የዐቃቤ ሕግ ድርሻ ምን ምን እንደሆኑ በኮድ መልክ ተዘጋጅተው ከአርባ ዓመታት በፊት በወጡት ዝርዝር መሠረታዊ ሕጎች እና ከዚያ በኋላ በየጊዜው የዐቃቤ ሕግ መስሪያ ቤቶችን ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግበራቸውን ለመወሰን በወጡት አዋጆች ተመልክተው እናገኛቸዋለን። በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ በፍትሐብሔር ዙሪያ ያሉትን ደርሻዎች በሁለት ከፍለን በዐቃብያነ ሕግ

[25] የፍትሕና የዴሞክራሲ ሥርዓት ሒደት በኢትዮጵያ፣1992፣አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ፣ ገጽ 368

ማቋቋሚያ አዋጆችና ከአዋጆቹ ውጭ ባሉ ሕጎች ለዐቃብያነ ሕግ የተሰጡ ፍትሐብሔር ነክ ሥልጣንና ተግባራት ብለን ማየት እንችላለን፡፡

7.1. በፍትሐብሔርና በንግድ ሕጎች ለዐቃብያነ ሕግ የተሠጡ ፍትሐብሔር ነክ ኃላፊነቶች፣

በ1950ዎቹ አካባቢ ጀምሮ ዐቃቤ ሕግ ከወንጀል ጉዳይ ባሻገር ያለውን ሚና ያካተቱ መሠረታዊ ሕጎች (Codes) ወጥተዋል ፡፡ በ1958 ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ አንቀጽ 42 ላይ ዐቃቤ ሕግ በሌሎች ሰዎች በተጀመሩ ክርክሮች ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ አንቀጹ

> “ ህግ የሚፈቅድለት በሆነ ጊዜ ሁሉ ዐቃቤ ሕጉ በነገሩ
> ጣልቃ ገብ ሆኖ ለመከራከር ይችላል፤ በተለይም ... ”

በማለት ዐቃቤ ሕግ ጣልቃ ሊገባ ስለሚችልባቸው አራት ሁኔታዎችን አመልክቷል፡፡ እነዚህም ሁኔታዎች ፡-

ሀ. ስለ ሰዎች መብት / የፍትሐብሔር ሕግ ከቁጥር 116-122፣ እና 156/

ለ. ችሎታ ስለማጣት / የፍትሐብሔር ሕግ ከቁጥር 234-354-377/

ሐ. ስለጋብቻ / የፍትሐብሔር ህግ ከቁጥር 592-608-609 እና 612/፣ እና

መ. ስለ ኪሣራ / የንግድ ህግ ቁጥር 975-978፣ 980፣ 1004 እና 1017/

ናቸው፡፡

ጣልቃ ገብነት በክርክር ተካፋይ ያልሆነ ወይም ያልነበረ እንግዳ ሰው በአንድ በተጀመረ ወይም በቀጠሮ ላይ ከሚገኝ ጉዳይ ጋር የተያያዘ የመብት ጥያቄ ወይም መቃወሚያ የሚያቀርብበት፣ በዚህም የተነሣ የክርክሩ ተካፋይ የሚሆንበት የሥነሥርዓት ሕግ ፅንሰ ሀሳብ ነው ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፡፡[26]

[26] Moore- Vestal: Moore’s Manual: Federal Practice and Procedure, Matthew Bender & Company incorporated ,1963 P. 943

የዚህ የጣልቃ ገብነት ሥነ ሥርዓት ሕግ ዕንሰ ሀሳብ ዓላማ አንድ በፍርድ ቤት በመታየት ላይ ያለና በሌሎች ሰዎች መካከል በመካሄድ ላይ ያለውን ክርክር ባለመስማቱ የተነሣ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነውን ሰው መብት ወይም ጥቅም እንዳይጐዳ ጥበቃ ለመስጠት ይቻል ዘንድ የክርክሩ ፍሬ ነገር በሆነው መብት ወይም ጥቅም ባለቤት ነኝ ወይም ድርሻ አለኝ ወይም ይመለከተኛል የሚል ሰው ክርክሩ እኔ በሌለሁበትና ክርክሬን ባላቀረብሁበት ሁኔታ ቢወሰን ይህን መብቴን ወይም ጥቅሜን የሚጎዳ ውሣኔ ሊሰጥብኝ ይችላል በማለት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን እንዲጠይቅና እንዲፈቀድለት ለማስቻል ነው፡፡

በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች አስቀድሞ የተጀመረ ክርክር እንኳ ቢሆን ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር የሚፈቀድለት ከሆነ ክርክሩ ያልተጀመረ ከሆነ ደግሞ ዐቃቤ ሕግ ክስ የመመስረት ሥልጣን ያለው መሆኑ የበለጠ ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ሮበርት አለን ሴድለር የተባሉት የሕግ ምሁር በዚህ አንቀፅ ሥር ስለተመለከተው የዐቃቤ ሕግ ጣልቃ ገብነት ሲያወሱ "በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ስለዐቃቤ ሕግ ጣልቃ ገብነት የተጠቀሰው እውነተኛ ጣልቃ ገብነት ሊባል አይችልም፡፡ ምክንያቱም የዐቃቤ ሕግ መስሪያ ቤት ከዚህ በላይ በተመለከቱት የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች ውስጥ እነዚህን ጉዳዮች በተመለከተ ራሱ ክስ መስርቶ እንዲከራከር መብት የተሰጠው በመሆኑ ነው፡፡ የሆነው ሆኖ ግን ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ክሶቹ በሌሎች ሰዎች የተጀመሩም ቢሆን የዐቃቤ ሕግ ጣልቃ ገብነት የተጠበቀ ነው"[27] በማለት ገልፀዋል፡፡

በመሆኑም የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ ካስቀመጠው የጣልቃ መግባት ጉዳይ ባሻገር የክርክሩ ባለቤት በመሆን ደረጃ ጭምር ዐቃቤ ሕግ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን አስመልክቶ ያለው ድርሻ በተለያዩ ጉዳዮች ዙሪያ ተደንግጎ እናገኘዋለን፡፡ እነዚህም ኃላፊነቶች፡-

[27] Robert Allen Sedler, Ethiopian Civil Procedure, Addis Ababa University, 1968,pp.99-100.

(1) በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 122 በተደነገገው መሠረት በክብር መዝገብ በስህተት የተጻፈ ነገር እንዲታረም ለፍርድ ቤት ተገቢውን አቤቱታ የማቅረብ ኃላፊነት፣

(2) በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 234 በተደነገገው መሠረት አካለመጠን ያላደረሰ ወይም በፍርድ ውሳኔ የተከለከለ ሰው አሳዳሪ ወይም ሞግዚት እንዲሻር ለፍርድ ቤት ተገቢውን አቤቱታ የማቅረብ ኃላፊነት፣

(3) በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 353(1) በተደነገገው መሠረት እብድ ወይም የፍትሐብሔር ሕጉ "ድውዮች" በማለት የሚፈርጃቸውን መናገር፣ መስማት ወይም ማየት የተሳናቸው በመሆናቸው ነዋሪ (ቋሚ) በሆነ እክል ምክንያት ራሳቸውን ችለው ለመተዳደር ወይም ንብረታቸውን ለማስተዳደር ችሎታ የላቸውም ለሚባሉ ሰዎች ሆኖ የፍርድ ቤት ክልከላ (judicial interdiction) እንዲሰጥ ለፍርድ ቤት ተገቢውን አቤቱታ የማቅረብ ኃላፊነት፣

(4) እብድ ወይም የፍትሐብሔር ሕጉ "ድውዮች" በማለት የሚፈርጃቸውን በተመለከተ የተሰጠ የፍርድ ቤት የክልከላ ትእዛዝ ተገቢ አይደለም ብሎ በሚያምንበት ጊዜ የተሠጠው የክልከላ ውሳኔ እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 355 እና 377(1) በተደነገገው መሠረት ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ ኃላፊነት፣ እንዲሁም አንድ በፍርድ ቤት የተከለከለ ሰው ለክልከላው ምክንያት የሆነው ጉዳይ የቀረ መሆኑን ሲገነዘብ የተጣለበት ክልከላ እንዲነሳለት ለፍርድ ቤት አቤቱታ የማቅረብ ኃላፊነት፣

(5) በሕግ የተከለከለ ሰው ከሥልጣኑ በላይ የሆነ ሕጋዊ ተግባር ፈፅሞ ሲገኝ ተግባሩ ያስከተለው ሕጋዊ ውጤት ፈራሽ እንዲሆን በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 387(2) በተደነገገው መሠረት ተገቢውን አቤቱታ ለፍርድ ቤት የማቅረብ ኃላፊነት፣

አንድ ሰው የወንጀል ድርጊት ፈፅሞ በፍርደ ቤት ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ ለፈፀመው ወንጀል ከሚጣልበት ቅጣት በተጨማሪ እንደ አግባብነቱ ሌሎች ተጨማሪ ቅጣቶች ሊጣሉበት ይችላሉ፡፡ እነዚህ ተጨማሪ ቅጣቶች የፈፀመውን ወንጀል ከባድነት እና የወንጀሉን ዓይነት እንዲሁም የአጥፊውን የወንጀል አፈጻጸም ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 123 መሠረት በፍርድ ቤቱ የሚወሰኑ ሲሆኑ የፍትሐብሔር ሕጉ የሕግ ክልከላዎች (legal interdiction) በማለት ይጠራቸዋል፡፡ ይህ ክልከላ የተለያዩ ጉዳዮችን ሊያካትት የሚችል ሲሆን ለምሳሌ አንድ ሰው ወላጅ በመሆኑ ምክንያት ያለውን የአስተዳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት መብት፣ የስራ ወይም የሙያ ፈቃድ አውጥቶ ሥራ የመስራት መብት፣ እማኝ ሆኖ በሰነዶች ላይ የመፈረም ወይም ዋስ ሆኖ የመቅረብ መብት፣ወ.ዘ.ተ. ሁሉ ይጨምራል፡፡

እነዚህን የሕግ ክልከላዎች በመተላለፍ አንድ ሰው አንድ ድርጊት ከፈፀመ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 459 ድንጋጌ መሠረት በወንጀል የሚጠየቅ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ግለሰቡ በሕግ የተጣለበትን ክልከላ በመተላለፍ የፈፀመው ተግባር ውጤት የሆኑትን ነገሮች ፈራሾች ናቸው፡፡ ይህን ሁኔታ ተከታትሎ ፈራሽ እንዲሆኑ ማድረግና መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነትም የዐቃቤ ሕግ ነው፡፡

(6) በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 592 (በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 18) በተደነገገው መሠረት ሕገ ወጥ የሆነ ጋብቻ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ተገቢውን አቤቱታ የማቅረብ ኃላፊነት ዐቃቤ ሕግ አለበት፡፡

(7) እንዲሁም በ1952 ዓ.ም በታወጀው የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ ቁጥር 975(ሐ) ላይ በተደነገገው መሰረት የነጋዴ መክሰር እንዲወሰን ተገቢውን አቤቱታ ዐቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት፡፡

በ1992 ዓ.ም በወጣው የተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 ከጋብቻ ጋር በተያያዙ በርካታ ጉዳዮች ዐቃቤ ሕግ ጣልቃ እንዲገባና ክስም እንዲመሰርት ደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት ዐቃቤ ሕግ አንድ ጋብቻ ከመፈፀሙ በፊት ጋብቻውን ለሚያስፈፅመው ባለሥልጣን ጋብቻው እንዳይፈፀም መቃወሚያ ማቅረብ

የሚችል ሲሆን ጋብቻው እንዳይፈፀም መቃወሚያው የሚቀርብበት ምክንያትም ተጋቢዎቹ ወይም ከተጋቢዎቹ አንዱ ጋብቻ ለማድረግ ሕጉ የሚፈቅደውን አነስተኛ ዕድሜ ስለማያሟላ፣ በተጋቢዎች መካከል የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና በመኖሩ፣ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ሊፈፀም በመሆኑ፣ ሁለቱም ተጋቢዎች ወይም ከተጋቢዎቹ አንዱ ጋብቻ ማድረግ እንዳይችል የሚያደርገው የፍርድ ክልከላ በመኖሩ ሊሆን ይችላል።[28]

ጋብቻው ከተፈፀመ በኋላም ጋብቻው እንዲፈርስ ዐቃቤ ሕግ በፍርድ ቤት ክስ መመስረት ወይም አቤቱታ ማቅረብ ይችላል። በመሆኑም ተጋቢዎቹ ወይም ከተጋቢዎቹ አንዱ ጋብቻ ለማድረግ ሕጉ የሚፈቅደውን አነስተኛ ዕድሜ የማያሟላ ሆኖ እያለ ጋብቻው ተፈፅሞ ከሆነ፣ በሥጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት ጋብቻ እንዳይፈፀም በሕግ የተደነገገውን ክልከላ በመተላለፍ ጋብቻ ተፈፅሞ ከተገኘ ፣ በጋብቻ ላይ ጋብቻ ተፈፅሞ የተገኘ እንደሆነ ዐቃቤ ሕግ በሁለት ሰዎች መካከል የተደረገው ጋብቻ እንዲፈርስ ክስ በመመስረት ጋብቻው እንዲፈርስ እንዲያደርግ በሕግ ኃላፊነት ተሰጥቶታል።[29] ይህም በፍትሐብሔር ሕጉና በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ በተለይ ከጋብቻ ጋር በተያያዘ የተመለከቱት ጉዳዮች በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግም ለዐቃቤ ሕግ የተሰጡ ጉዳዮች በመሆናቸው አሁንም ዐቃቤ ሕግ በጉዳዮቹ ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ አስፈላጊ መሆኑ የታመነበት መሆኑን የሚያመለክት ነው።

7.2. በዐቃብያነ ሕግ መስሪያ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጆች ለዐቃብያነ ሕግ የተሠጡ ፍትሐብሔር ነክ ኃላፊነቶች፣

ቀደም ባለው ክፍል በፍትሐብሔር እና በንግድ ሕጎች በሌሎች ሰዎች እየተካሄዱ ባሉ ክርክሮች ዐቃቤ ሕግ ጣልቃ ስለሚገባበት ሁኔታ በጥቅሉ እና በግልፅ ተመልክተው በተቀመጡ ጉዳዮች ላይ ዐቃቤ ሕግ የፍትሐበሔር ክስ (አቤቱታ) ለፍርድ ቤት ሊያቀርብ ስለሚችልበት ሁኔታ በአጭሩ ተመልክተናል። ከዚህ በመቀጠል የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግሥት አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 471/98 አንቀፅ

[28] የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 18 እና 19ን ይመለከቷል።
[29] የተሻሻለውን የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 31፣32 እና 33፤

23 ሥር እና በሌሎች በክልል መስተዳድር አካላት አዋጆች ለፍትሕ ሚኒስቴር (ለፌዴራል ዐቃቤ ሕግ) እና ለፍትሕ ቢሮዎች (ለክልል ዐቃብያነ ሕግ) የተሰጡ ፍትሐብሔር ነክ ኃላፊነቶችን እንመለከታለን፡፡

አዋጅ ቁጥር 471/98 አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 7 ፍትሕ ሚኒስቴር (የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ) "የሕዝቡን እንዲሁም የፌደራል መንግሥትን መብትና ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በፌዴራልና በክልል ፍ/ቤቶች በማናቸውም ዳኝነት ሰሚ አካል ወይም የሽምግልና ጉባዔ ክስ ይመሰርታል፣ ክስ እንዲመሠረት ያደርጋል፣ ወይም ጣልቃ በመግባት ይከራከራል" በማለት ይደነግጋል፡፡ የክልል ዐቃብያነ ሕግን ሥልጣንና ተግባር የሚወስኑት የየክልሎቹ አዋጆችም በተመሳሳይ ዐቃቤ ሕግ የመንግስትንና የሕዝብን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ ያለበትን ኃላፊነት ይደነግጋሉ፡፡ ከዚህም አንጻር ለምሳሌ የአማራ ክልል ዐቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባር የሚወስነውን አዋጅ ቁጥር 4/85 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 11ን ብንመለከት "የክልሉን ሕዝብ መብትና ጥቅም ለማስከበር አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በፍትሐብሔር ጉዳይ ጣልቃ መግባት" ተብሎ ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶት እናገኘዋለን፡፡

በመሠረቱ የሕዝብ እንዲሁም የመንግስት መብትና ጥቅም የሚባሉት እነዚህ እነዚህ ናቸው ብሎ በዝርዝር ማስቀመጥ የሚቻል አይደለም ወይም ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡ ነገር ግን በአጠቃላይ ሲታይ እነዚህ ጉዳዮች ማንኛውም ሰው እንዲያከብራቸውና እንዳይጋፋቸው በሕግ የተዘረዘሩ ሆነው በእነዚህ ላይ የሚደርሰው ጥቃት የመንግሥትንም ሆነ የአጠቃላዩን ህብረተሰብ ወይም የተወሰነውን የህብረተሰብ ክፍል ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መብትና ጥቅም የሚነኩ ጉዳዮች ናቸው ተብለው ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ በግለሰቦች መካከል በመንግሥት ወይም በህዝብ ጥቅም ላይ ከሚደረጉ ድርጊቶች (Juridical Acts) የሚመነጩ የግለሰቦች ክርክሮች (ለምሣሌ በስጦታም ሆነ በሽያጭ በግለሰብም ሆነ በመንግሥት አካላት አማካኝነት ለሶስተኛ ወገኖች ሊተላለፉ በማይችሉ "ለሕዝብ አገልግሎት በተመደቡ ሀብቶች" (public Domain) ላይ የሚደረጉ ውሎች ሊሆኑ የሚችሉ ሲሆን በእነዚህ ክርክሮች የሚቀርቡት ክርክሮችና በዚህም መሠረት የሚሰጥ ውሣኔ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የመንግሥትንም ሆነ የሕዝቡን መብትና ጥቅም ሊነኩ ይችላሉ፡፡ መንግሥት ወይም

እርሱ የሚወክለው አካል (ዐቃቤ ሕግ) በእነዚህ ጉዳዮች ጣልቃ እንዲገባ የሚያስፈልግበት ዋና ምክንያት ሀገሪቱ በምትተዳደርባቸው ሕጎች መሠረት መንግሥት የእያንዳንዱን የነብረተሰብ ክፍል እና ግለሰብ መብትና ጥቅም ከማክበርና ከማስከበር በተጨማሪ የአጠቃላዩን ህብረተሰብ መብትና ጥቅምም የመጠበቅና የማስከበር ሕገ መንግሥታዊ ኃላፊነቱና ግዴታውም በመሆኑ ነው፡፡ ይህ መንግሥታዊ ግዴታ ደግሞ አገራችን በምትከተለው ፌዴራላዊ የመንግሥት አወቃቀር ሥርዓት ምክንያት በፌዴራል መንግሥቱና በክልል መንግሥታት ላይ የወደቀ ኃላፊነት ነው፡፡

የሕዝቡንና የመንግስትን መብትና ጥቅም የሚነካ ተግባር ሲፈፀም መብትና ጥቅሙ እንዲከበር ራሱንና ህብረተሰቡን በመወከል ክስ የሚመሰርተውና የሚከራከረው መንግሥት ራሱ ነው፡፡ መንግሥት ያለበትን ይህን ኃላፊነት የሚወጣው ደግሞ ለዚሁ ዓላማ ባቋቋመው ተቋም (በዐቃቤ ሕግ) አማካኝነት ነው፡፡ ማለትም ከየትኛውም አካል በላይ በእነዚህ የፍትሐብሔር ጉዳዮች መንግሥት እና ህብረተሰቡ የባለቤትነት ወይም የበለጠ መብትና ጥቅም ያላቸው በመሆኑ ይህን መብትና ጥቅም እንዲያስከብር በዚህ ዙሪያ ውክልና የተሰጠው ዐቃቤ ሕግ ሥልጣንና ተግባር አግባብነት መታየት ያለበትም ከዚህ አኳያ ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው ኃላፊነቱ በተጨማሪ በአዋጅ ቁጥር 471/98 አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 6 ላይ እንደተደነገገው ፍትሕ ሚኒስቴር (የፌዴራል ዐቃቤ ሕግ) በወንጀል ድርጊት እና በሰብዓዊ መብት መጣስ ምክንያት ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው ክስ ለመመስረት አቅም ለሌላቸው ግለሰቦች ካሳ እንዲያገኙ በፍትሐብሔር ክስ የመርዳት ኃላፊነት ተጥሎበታል፡፡ ከዚህ አንጻርም እንዲሁ ለምሳሌ የኦሮሚያ ክልል ፍትሕ ቢሮ ሥልጣንና ተግባር የሚወስነውን አዋጅ ቁጥር 87/97 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 19ትን ብንመለከት “በወንጀል ድርጊት ጥቃት ምክንያት ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶባቸው ክስ ለመመስረትም ሆነ ለመከራከር አቅም ለሚያንሳቸው ካሳ እንዲያገኙ በፍትሐብሔር ክስ እገዛ ያደርግላቸዋል” ተብሎ ሥልጣንና ተግባር ተሰጥቶት እናገኘዋለን፡፡

በ1949 ዓ.ም የወጣው የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በአንቀፅ 100 ንዑስ ቁጥር (1) ሥር በወንጀል ጉዳት የተነሳ በተበዳዩ ወይም በተበዳዩ ባለመብቶች ላይ

ስለሚደርሱና ካሣ ሊጠየቁባቸው ስለሚችሉ ጉዳቶች የሚገልፅ ሲሆን ከእነዚህም ዋናዎቹ የሞት አደጋ፣ ሰውነትን ወይም ጤንነትን የማጉደል፣ ክብርን የመንካት፣ ንብረት የማፍረስ ወይም ሀብትን የመጉዳት ጉዳቶች እንደሆኑና የካሣ ጥያቄው ከእነዚህ በተጨማሪ የሆስፒታልና የመታመሚያ ወጪን እንደሚጨምር ይደነግጋል። እንዲህም በሆነ ጊዜ ጉዳት አድራሹ ያጠፋውን ወይም ያፈረሰውን እንደነበረ በመመለስና በዚህ መልክ ለመፈፀም በማይቻሉ ጉዳቶች ደግሞ ተመጣጣኝነት ያለው ካሣ /ገንዘብ/ በመክፈል የተበደሉትን ሰዎች የመካስ ግዴታ እንዳለበትም ይኸው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አንቀፅ 100(1) ይደነግጋል።

በዚህም መሠረት አንድ ሰው ለፈፀመው ወንጀል በሕግ የሚቀጣ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለበደለው ሰው ወይም ለተበደለው ቤተሰብ ካሣ የመክፈል ግዴታ ዕውቅና ያለውና የሕግ ማዕቀፍም የተበጀለት ጉዳይ ነው።

ይሁን እንጂ በተፈፀመበት የወንጀል ድርጊት ምክንያት የተለያየ ዓይነት በደል የደረሰበት ሰው ይህን በደሉን የፈፀመበትን ሰው ለሕግ አቅርቦ ካሣውን እንዲከፍለው ለመጠየቅ መብት ያለው ለመሆኑ በሕግ ተደንግጐ የሚገኝ ቢሆንም በተበዳዮች ዘንድ እምብዛም የሚታወቅ ባለመሆኑ፣ በደለኛውን ሰው በፍርድ ቤት ከስሶ ካሣ ለመጠየቅ በተጐጂው ላይ ተጨማሪ ወጪን የሚጠይቅ በመሆኑና ተጐጂው ይህን ወጪ ለመሸፈን አቅም ስለማይኖረው የተበደሉ ወገኖች በዚህ መብታቸው ተጠቅመው ካሣ የሚያገኙበት ሁኔታ በጣም ውሱን እንደሆነ በደፈናው መናገር ይቻላል። ይህ ደግሞ በወንጀል ድርጊት ምክንያት የተጎዳው ሰው የሚገባውን ካሳ ሳያገኝ እንዲቀር የሚያደርግ በመሆኑ ጉዳት አድራሹ በፈፀመው የወንጀል ድርጊት ምክንያት ላደረሰው ጉዳት ተጠያቂ ሳይሆን እንዲቀር የሚያደርግና ድርጊቱ ያስከተለውን ኪሣራ ሌላ ሰው ተሸክሞት እንዲቀር የሚያደርግ ነው። የመጨረሻ ውጤቱም ወንጀል ፈጻሚዎች "የሥራቸውን ስለማያገኙ"[30] ወንጀል ለመፈፀም ይበረታታሉ ሊባል ባይችልም እንኳን ሊድረስባቸው የሚገባውን ኪሣራ ያህል ያልደረሰባቸው በመሆኑ ለወደፊቱ ወንጀል እንዳይፈፅሙ በቂ የሆነ ትምህርት አላገኙበትም ተብሎ ሊወሰድ የሚችል ከመሆኑም በላይ ፍትሐዊም አይደለም። በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የሕዝብና የመንግሥት ጥቅም አለ። ለዚህም

[30] በወንጀል የሚጠየቁ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው።

ነው የዐቃቤ ሕግ በጉዳዩ ውስጥ መግባት ተገቢ የሚሆነው፡፡ በዚህም መሠረት ዐቃቤ ሕግ በፍትሐብሔር ክርክር ጉዳዩ ውስጥ የሚካፈለው የሕዝቡን ወይም በወንጀል ድርጊት ሳቢያ ሰለባ የሆኑትን ግለሰቦች ሕጋዊ መብትና ጥቅም ለማስከበር ነው፡፡ ይህ በሕግ ለዐቃቤ ሕግ በፍትሐብሔር ጉዳይ ዙሪያ የተሰጠው ውክልና እንደሌሎች በግለሰብ ውክልና እንደሚንቀሳቀሱ ጠበቆች የሚታይ አይደለም፡፡ እንደዚህ ባሉ የፍትሐብሔር ጉዳዮች ዙሪያ የተሰጠው የዐቃቤ ሕግ ሚና ሕግን ከማስከበር እና አጠቃላይ የመንግስትንና የሕዝቡን መብትና ጥቅም ከማስጠበቅና ከማስከበር አንጻር ብቻ መታየት ያለበት ነው ፡፡

በኢትዮጵያ በወንጀል ድርጊት ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ካሳ እንዲያገኙ በፍትሐብሔር ረገድ የመርዳት ኃላፊነት ለመጀመሪያ ጊዜ በህግ ተቀርፆ የወጣው በ1980 ዓ.ም የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤትን ለማቋቋም ወጥቶ በነበረው አዋጅ ቁጥር 11/80 ሲሆን ይህ ኃላፊነትም የተሰጠው ለዚሁ የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መሥሪያ ቤት ነበር፡፡ ኃላፊነት ለተጠቀሰው መሥሪያ ቤት የሚሰጠው የአዋጁ አንቀፅ 10(13) ኃይለ ቃል፡-

> “ በወንጀል ድርጊት ከባድ የአካል ጉዳት ደርሶባቸው ክስ ለመመሥረትና ለመከራከር አቅም ለሌላቸው ግለሰቦች ካሣ እንዲያገኙ በፍትሐብሔር ክስ መርዳት...”

የሚል ነው፡፡

በዚህ ድንጋጌ መሠረት ዐቃቤ ሕግ በወንጀል ድርጊት ለሚደርስባቸው ጉዳት ካሣ ለመጠየቅ የገንዘብ አቅም ስለሌላቸው የፍትሐብሔር ክስ በመመሥረት ካሣ እንዲያገኙ የሙያ ድጋፍ የሚሰጣቸው ሰዎች የድጋፉ ተጠቃሚ የሚሆኑት እነዚህ ሰዎች የተፈፀመባቸው የወንጀል ድርጊት የአካል ጉዳት ያስከተለባቸው ሆነው የተገኙ እንደሆነ እና ይህ የአካል ጉዳታቸውም "ከባድ" ነው የተባለላቸው እንደሆነ ብቻ ነበር፡፡ በዚህም መሠረት የወንጀሉ ድርጊት የቱንም ያህል ከባድ የንብረትና የገንዘብ ጉዳት ቢያስከትል የአካል ጉዳት ያልደረሰባቸው ተጐጂዎች በፍትሐብሔር ክስ ካሣ ለማግኘት የዐቃቤ ሕግን የሙያ ድጋፍ ለማግኘት አይችሉም ነበር፡፡ (የፍትሐብሔር ክሳቸውን ለመመሥረት ለዳኝነትም ሆነ ለጠበቃ መክፈል የማይችሉ መሆናቸው ቢረጋገጥ/

የሚታመንበት ቢሆንም እንኳ)። ይህን የ1980 ዓ.ምን አዋጅ የሻረው አዋጅ ቁጥር 39/1985ም አንቀፅ 9(9)ም በተመሳሳይ መልኩ ይደነግግ ነበር።

አሁን ሥራ ላይ ባሉት ድንጋጌዎች መሠረት ግን ዐቃቤ ሕግ የሙያ ድጋፍ የሚሰጣቸው ሰዎች በወንጀል ድርጊት የተነሳ ከባድ ጉዳት የደረሰባቸው ሊሆኑ የሚገባ ሲሆን ይህ "ከባድ ጉዳት" ግን ቀድም ሲል በነበሩት ድንጋጌዎች እንደተገለፀው " ከባድ የአካል ጉዳት" ብቻ ያልተባለ በመሆኑ የዐቃቤ ሕግ ድጋፍ በወንጀል ድርጊት የተነሳ ሊደርስ የሚችለውንና ከባድ ሊባል የሚችለውን የጉዳት ዓይነት ሁሉ ሊጨምር ይችላል። ምናልባት ይህ የተደረገው ከላይ የተጠቀሰውና የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 100 ድንጋጌ ፍትሐብሔር ካሳው የሕይወት፣ የአካል ጉዳትና የንብረት ጉዳት ካሳን ሁሉ የሚጨምር ሆኖ እያለና ለደረሰባቸው ጉዳት በግል ክስ ለማቅረብ የማይችሉ ሰዎች በአካል ጉዳት የሚጠይቁትን ካሳ ብቻ በዐቃቤ ሕግ ድጋፍ እንዲሰጣቸው ማድረግና ስለንብረታቸው የሚጠይቁትን ካሳ በግላቸው እንዲያቀርቡ ከማድረግ ማንኛውንም ጉዳት በዐቃቤ ሕግ ድጋፍ እንዲቀርብ ማድረጉ ተገቢነት ያለው መሆኑ ስለታመነበት እንደሆነ መገመት ይቻላል።

የዐቃቤ ሕግ ድጋፍ በወንጀል ድርጊት ከባድ ጉዳት ደርሶባቸው[31] በፍትሐብሔር ከሰው ካሳ ለማግኘት የማይችሉትን የፍትሐብሔር ክስ እንዲመሠርቱ በማስቻል ካሳ እንዲያገኙ ማድረግን ያለመ ሲሆን ይህም የፍትሐብሔር ክስ ስለሚመሠርቱበት ሁኔታ ከማማከር፣ የፍትሐብሔር ክስ አዘጋጅቶ እስከመስጠትና ተጎጂውን በመወከል አግባብ ላላቸው ፍርድ ቤቶች ክሱን እስከማቅረብ እና እስከ መከራከር፣ እንዲሁም ክሱ ወይም ክርክሩ ተቀባይነት ካላገኘ በይግባኝ እስከ መውሰድ፣ለተጎጂው በተፈረደ ጊዜም በአፈጻጸሙ ረገድ ተገቢውን በማድረግ ካሳ እስከማስገኘት ድረስ ሊደርስ ይችላል።

[31] ለፍትሕ ሚኒስቴር በአዋጅ ቁጥር 471/98 ካሳ ለማግኘት የማይችሉትን ሰዎች መርዳትን አስመልክቶ የተሰጠው ኃላፊነት በወንጀል ድርጊት ብቻ ሳይሆን በሰብዓዊ መብት መጣስ ምክንያት ከባድ ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎችም ጭምር የሚመለከት ነው።